# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ (ኢፌዴሪ) ረቂቅ "የወንጀል ሥነ ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ"ን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) የቀረበ የማሻሻያ ምክረ ሃሳቦች

**ታህሳስ 2013**

## መግቢያ

### 1.1. ስለ ወንጀል ሥነ ሥርዓትና የሰብዓዊ መብቶች የሕግ ማዕቀፎች

ረቂቅ ሕጉ ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር ያሉት በጎ ጎኖችና ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ምክረ ሃሳቦች ከማቅረባችን በፊት ሰብአዊ መብቶች ከወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ጋር ያላቸውን ግንኙነትና የወንጀል ፍትሕን ለማረጋገጥ የሚኖራቸውን ሚና በጥቂቱ መዳሰስ በዚህ ሰነድ የተካተቱን ዝርዝር ነጥቦች የበለጠ ለመረዳት ያስችላል።

በሕግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ማህበረሰብ የመፍጠር ዓላማን ለማሳካት ከሚረዱ መሳሪያዎች መካካል ከጠቅላላው የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ማዕቀፍ አንዱ የሆነው የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ ይገኝበታል። የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ በአንድ በኩል የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥና በሌላ በኩል ዲሞክራሲን በማስፈን ጥረት በግለሰቦችና በጠቅላላው ማህበረሰብ መብቶችና ፍላጎቶች መካካል ሊፈጠር የሚችለውን ተቃርኖ ለማረቅ ብሎም እርስ በርስ ይደጋገፉ ዘንድ ከሚያስችሉ የሥርዓት መሣሪያዎች መካከል ዋነኛው ነው። ሁለቱን ዕሴቶችና ፍላጎቶች አጣጥሞ የሚያሳካ የወንጀል ፍትህ ሥርዓት ሕግ፤ አስፈጻሚ አካላት የወንጀል ድርጊቶችን በሚመለከት ያላቸውን ኃላፊነት በሕጋዊ አግባብ ብቻ እንዲጠቀሙ የሚያስችልና በአንጻሩ በምርመራ፣ በመያዝና አጥፊዎችን በመቅጣት ሂደት ሥልጣንን ያለአግባብ ተጠቅሞ የግለሰቦች መብቶችና ነጻነቶች ላይ አላስፈላጊ ጫና ሳይፈጠር በቂ ጥበቃ የሚያደርግ መሆን ይኖርበታል። የወንጀል ፍትህ ሥርዓቱ እነኚህን ተቃርኖዎች ሊያስታርቅ የሚችለው ደግሞ እውነትን ለማውጣት ያለመ ሲሆንና፣ ይህንንም ለማሳካት ፍትሃዊ መንገዶችን ሲጠቀም እንዲሁም የፍትህ አካላት የሰብዓዊ መብቶች የሕግ ማዕቀፎች የሚያስቀምጧቸውን መርሆች ባከበረ መልኩ ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ማድረግ ሲችል ነው። እነዚህም ጠቅላላ መርሆች የሕጋዊነት፣ የጥብቅ አስፈላጊነት፣ የተመጣጣኝነት፣ መድልዎና አግላይነትን የመከላከል ናቸው።

ይህ ሰነድ ከላይ የተጠቀሱትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ረቂቅ የወንጀል ሥነ ሥርዓትና የማስረጃ ሕጉን በሚከተለው መልኩ ይዳስሳል።

### 1.2. ስለ ማርቀቅና ግብዓት ማሰብሰብ ሂደት

ረቂቅ ሕጉ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርምሮ ከመጽደቁ በፊት የምክር ቤቱ የሕግ፣ ፍትህ እና ዲሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የባለ ድርሻ አካላትን በማሳተፍ ግብዓት ለመቀበል ያለመ የምክክር መድረክ ታሕሳስ 12 ቀን 2013 ዓ.ም. ማዘጋጀቱ ይታወሳል። በዚህም መድረክ ኢሰመኮን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ተገኝተው ያሏቸውን አስተያየቶች ለቋሚ ኮሚቴው በቃል ያስረዱ ሲሆን ተጨማሪ አስተያየቶችን በጽሁፍ የማቅረብ ሂደቱም ቀጥሏል፡፡

ዜጎች በሕግ እና ፓሊሲ ማርቀቅ እንዲሁም በሌሎች ውሳኔ አሰጣጥ ሒደቶች ተሳትፎ የማድረግና ድምጻቸውን የማሰማት መብታቸውን ታሳቢ በማድረግ ኢሰመኮ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ የሲቪል ማህበራት ተወካዮችንና በወንጀል ሕግ ላይ ሙያዊ እውቀትና ልምድ ያዳበሩ ባለሙያዎችን ያሳተፈ የምክክር መድረክ በታህሳስ 21 ቀን 2013 ዓ.ም. አዘጋጅቷል። በዚህም የምክክር መድረክ ኢሰመኮ በረቂቅ ሕጉ ላይ ያደረገውን ጥናትና በዘርፉ ባለሙያ የቀረበውን የመነሻ ጽሁፍ መሠረት በማድረግ ረቂቅ ሕጉ ከሴቶች፣ ከህጻናትና ከአካል ጉዳተኞች መብቶችና ከጠቅላላ የሰብዓዊ መብቶች የሕግ ማዕቀፍ አንጻር ያለውን ጠንካራ ጎኖችና ሊሻሻሉ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ተጨማሪ ግብዓት ወስዷል።

ይህ ሰነድ ኢሰመኮና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ረቂቅ ሕጉ ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር እንዲሻሻሉ በሚል የተሰጡትን ምክረ ሃሳቦችም መሰረት አድርጎ የሚያቀርብ ነው። ረቂቅ ሕጉን ለመተንተንና ምክረ ሃሳብ ለማቅረብ የኢፌዴሪ ሕገ መንግስትን እንዲሁም ኢትዮጵያ ተቀብላ ያጸደቀቻቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች፣ መርሆችና ትንታኔዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ምንም እንኳን ኢሰመኮ በዚህ ሰነድ አማካኝነት ረቂቅ ሕጉ ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር ሊሻሻሉ የሚገባቸውን በርካታ ነጥቦች የሚያነሳ ቢሆንም ረቂቅ ሕጉ በተወካዮች ምክር ቤት ከመጽደቁ በፊት የሚደረጉት ምክክሮች የበለጠ ተጠናክረው መቀጠላቸው ጠቃሚና አስፈላጊ ነው።

## 1.3 የረቂቅ  ሕጉ አንኳር ጠንካራ ጎኖች

የኢፌዴሪ ረቂቅ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ እና የማስረጃ ሕግ በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ሕጎችን፣ ጽንሰ ሃሳቦችን እንዲሁም መርሆችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ድንጋጌዎችን ያካተተ ነው። በ1961 ዓ.ም. ጸድቆ እስካሁን በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ የሚተችባቸውን ክፍተቶችንም ለማስተካከል ጉልህ ጥረት ያደረገ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል።

ከረቂቅ ሕጉ ጠንካራ ጎኖች መካከል የወንጀል ሥነ ሥርዓት ዓላማን በግልጽ ማስቀመጡና እነኝህም በወንጀል ምርመራ፣ ክስ፣ ፍርድ ሂደትና አፈጻጸም በሕገ መንግስቱ የተረጋገጡ ሰብዓዊ መብቶችን ማክበር እና ማስከበር መሆኑ ለሰብዓዊ መብቶች የተሰጠውን ከፍተኛ ግምት የሚያሳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱ እውነትን የማውጣትና የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ዓላማዎችን ማካተቱ ትክክል ነው። ሊስተካከሉ የሚገቡ ድንጋጌዎች ቢኖሩም በመርህ ደረጃ የወንጀል ምርመራ

መካሄድና መጠናቀቅ ያለበት አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ተጠርጣሪው ሳይያዝ መሆን እንዳለበት በግልጽ መደንገጉ እንዲሁም ለወንጀል ምርመራና ክስ መመስረት የጊዜ ወሰኖች ማስቀመጡ የረቂቅ ሕጉ ጠንካራ ጎኖች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መልኩ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በመያዝና በእስር ወቅት ሕግ አስፈጻሚ አካላት ኃይልን በሚጠቀሙበት ወቅት የተመጣጣኝነት መርሆችን ባከበረ መልኩ መሆኑን በግልጽ ማመላከቱ የረቂቅ ሕጉ ጥሩ ጎን ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ከሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ አንጻር ከሚነቀፍበት ጉዳዮች አንዱ በስህተት ወይም ያለ በቂ ማስረጃ ወንጀል ፈጽሟል በሚል የፍርድ ቅጣት የተላለፈበት ግለሰብ ከፍርድ በኋላ ንጹህነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ቢችል እንኳን በአመክሮ ወይም በይቅርታ ካልተፈታ በስተቀር የሚለቀቅበትን አሰራር አለማስቀመጡ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ረቂቅ ሕጉ ያላግባብ የጥፋተኛነት ውሳኔ የተላለፈባቸውንና በእስር ላይ ያሉ ግለሰቦችን ጉዳይ ፍርድን በመከለስ ሂደት እንደገና እንዲታይ የሚያስችል እና ካሳ የማግኘት መብትን የሚያረጋግጥ ሥነ ሥርዓት ማስቀመጡ ያለ ሕግ አግባብ በነጻነት የመንቀሳቀስ ነጻነትን ያለመገፈፍ መብትንና ከዚህ መብት ጋር ተያያዥ የሆኑ በርካታ መብቶችን ለማስከበርና ለማስጠበቅ የሚያስችል በጎ ጎን ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መሻሻል የሚገባቸው ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የተከሳሾችን ከፍርድ በፊት ነጻ ሆኖ የመገመት፣ በጠበቃ ወይም በሕግ አማካሪ የመወከል መብትን እንዲሁም በወንጀል ሂደት የሚሳተፉ ከሳሾችና ተከሳሾች እኩል ሆኖ የመታየት መርሆችን (መብትን) በግልጽ ማስቀመጡ የሚያበረታታ ነው፡፡

የወንጀል ተጠርጣሪዎችን፣ የተከሳሾችን፣ የፍርደኞችን እንዲሁም በፍትህ ሥርዓቱ ተሳታፊ የሆኑ ሰዎችን ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብርን ከሚያዋርድ አያያዝ የመጠበቅ ሰብዓዊ መብትን የሚያረጋግጥ ክልከላ ማስቀመጡ ሌላው የረቂቅ ሕጉ ጠንካራ ጎን ነው፡፡ ሆኖም ኢሰመኮ ለዚህ መብት በተሻለ ጥበቃ ለማድረግ የሚያስችሉ ዝርዝር አስተያየቶች በሰነዱ አካቷል፡፡

በወንጀል ድርጊት የጥፋተኛነት ውሳኔ ተላልፎባቸው የእስራት ቅጣታቸውን ፈጽመው ከማረሚያ ቤት የሚወጡ ሰዎች በቀላሉ ወደ ቤተሰቦቻቸው እና ህብረተሰቡ መቀላቀል እንዲችሉና የመልሶ ማቋቋም አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችላቸውን አሠራር ማስመቀመጡ የረቂቅ ሕጉ ጠንካራ ጎን ነው፡፡ በተያያዥነት የወንጀል ኃላፊነታቸው የተረጋገጠ ሰዎች ከጤናቸው ሁኔታ፣ ከሞያቸው፣ ከስራቸው አስፈላጊነት ወይም አይተኬነት የተነሳ ወይም በሌላ ምክንያት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የእስራት ቅጣታቸውን አፈጻጸም ለተወሰነ ጊዜ ለማስተላለፍ የሚያስችል አማራጭ ሥርዓት ማስቀመጡ የረቂቅ ሕጉ ሌላው በጎ ጎን ነው፡፡

## 1.4 የረቂቅ ሕጉ አንኳር ክፍተቶች

ጠቅለል ባለ መልኩ ረቂቅ ሕጉ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክፍተት ያለው በመሆኑ በሚቀጥለው የሰነዱ ክፍል በተሰጡት ምክረ ሃሳቦች መሠረት ሊሻሻል ይገባል፡-

- ስለ መያዝ፣ መታሰር፣ ኃይል አጠቃቀምና የቃል አቀባበልን የሚመለከቱት ድንጋጌዎች በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋት ማዕቀፍ የወጡ አግባብነት ያላቸውን መስፈርቶች (መለኪያዎች) ባሟላ መልኩ መስተካከል እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ተደራሽ የሆነ የኃይል አጠቃቀምና ቅሬታ የማቅረቢያ ሥነ ሥርዓት ሊካተት ይገባል፣
- ረቂቅ ሕጉ የኃይል አጠቃቀምን በሚመለከት ከተመጣጣኝነት መርሆ በተጨማሪ፡ ጥንቃቄ የማድረግ፣ የህጋዊነት፣ የጥብቅ አስፈላጊነት፣ አድልዎ ያለማድረግ መርሆዎችን (principles of precaution, legality, necessity, proportionality and non-discrimination) ሊያካትት ይገባል፣
- የወንጀል ምርመራን ተጠርጣሪን ከመያዝ በፊት ስለማጠናቀቅ በረቂቅ ሕጉ የተመለከተው አጠቃላይ መርሆ ቢኖርም ሌሎች ከመያዝ እና ምርመራ ጋር የተያያዙ የረቂቁ ድንጋጌዎች ይህን መርህ የሚሸረሽሩ በመሆናቸው፤ በምክረ ሃሳቦቹ የተመለከቱ ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል፣ በተለይም ከፍርድ በፊት የሚደረጉ ተጠርጣሪን ወይም ተከሳሽን የመያዝና የማሰር ሥርዓቶች በተቻለ መጠን በልዩ ሁኔታዎች ብቻ እንዲሆኑ አስፈላጊው ማሻሻያ ሊደረግ ይገባል፣

- በዋስትና የመለቀቅ ትዕዛዝ ላይ ዐቃቤ ሕግ ይግባኝ የማለት ሥርዓት ቀሪ ሊሆን ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ ነፍሰ ጡር ለሆነች ሴት ወይም ከ9 ዓመት በታች የሆነ ሕፃን ወይም የምትንከባከበው የአካል ጉዳተኛ ላላት እናት ዋስትና ወዲያውኑ እንዲፈቀድላት የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፣

- በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት የተደነገገው ሌሎች በአለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሕግጋት የተመለከቱ የፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መስፈርቶች በሚያሟላ መልኩ ሊስተካከል ይገባል፣

- በምርመራ ወቅት ናሙና አለመስጠት የተጠርጣሪውን ጥፋተኛነት የሚያረጋግጥ እንደሆነ የሕግ ግምት የሚወስደው ድንጋጌ በራስ ላይ ያለመመስከር (ራስን ያለመወንጀል) መብትን እንዲሁም የዐቃቤ ሕግን ጥፋተኝነትን ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ኃላፊነት ስለሚፃረር ሊሰረዝ ይገባዋል፣
- ረቂቅ ሕጉ ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን (ህጻናት፣ ወጣት አጥፊዎች፣ የጾታ ጥቃት ተጋላጮች፣ አካል ጉዳተኞች እና ሌሎች) መብቶችንና ፍላጎቶችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ድንጋጌዎች ቢታከሉበት፤ በተለይም በመያዝ፣ በወንጀል ምርመራ፣ በምስክርነት

አሰጣጥ እንዲሁም በዋስትና የመለቀቅ ጉዳዮችን የሚመለከቱ የረቂቅ ሕጉ ድንጋጌዎች አስፈላጊው ማስተካከያ ሊደረግባቸው ይገባል፣

- የልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴዎችን የሚመለከቱ የረቂቁ ሕግ ድንጋጌዎች የሰዎችን የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ ሰብዓዊ መብት ላይ አላስፈላጊ ጫና በማይፈጥር መልኩ ሊቀረፁና ከሕጉ አፋፃፀም ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ችግሮችም ግልጽ፣ ተደራሽና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የቅሬታ ማቅረቢያና አስተዳደራዊ የቁጥጥር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፣
- የጥፋተኝነት ድርድር የሚመለከቱት እንዲሁም ስለባህላዊ የዳኝነት ሥርዓቶች የሚመለከቱት ድንጋጌዎች በሰፊው የተቀረፁ እና በሰብአዊ መብቶች ላይ አላስፋላጊ ጫና ሊጥሉ ስለሚችሉ በተሰጡት ምክረ ሃሳቦች መሰረት ሊስተካከሉ ይገባል።

ዝርዝሩ እንደሚከተለው በሰነዱ ሁለተኛ ክፍል ከእነምክረ ሃሰቡና ሃተታ ዘ-ምክንያት ጭምር ቀርቧል፡

| ተ.ቁ. | የተዳሰሰው ድንጋጌ (አንቀጽ) ይዘት | በደንጋጌው ላይ የቀረበ አስተያየት፣ ምልከታ፣ እና የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ | የምልከታው (ምክረ ሃሳቡ) ሃተታ ዘ-ምክንያት ወይም ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| 1. | አንቀጽ ፮ በአንድ ወንጀል ድጋሚ ክስ ስለመከልከሉ<br><br>ማንኛውም ሰው በዚህ ሕግ እና በወንጀል ሕግ መሠረት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም ሌላ ሕጋዊ ርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት የወንጀል ድርጊት እንደገና አይከሰስም ፡፡ | ድንጋጌው በሚከተለው መልኩ ሊስተካከል ይገባል፡<br><br>አንቀጽ ፮ በአንድ ወንጀል ድጋሚ **ቅጣት** ስለመከልከሉ<br><br>ማንኛውም ሰው በዚህ ሕግ እና በወንጀል ሕግ መሠረት የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ ተረጋግጦ በተቀጣበት ወይም ሌላ ሕጋዊ ርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት የወንጀል ድርጊት እንደገና አይከሰስም **ወይም አይቀጣም፡፡** | የኢፌዲሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 23 “በአንድ ወንጀል ድጋሚ **ቅጣት** ስለመከልከሉ” የሚለውን አገላለፅ የሚጠቀም በመሆኑና ይህ አገላለፅ “ድጋሚ ክስ ስለመከልከሉ” ከሚለው በተሻለ በኢንግሊዝኛው “prohibition of double jeopardy” የተባለውን ፅንሰ ሃሳብ በተሻለ መልኩ ይወክላል። በተመሳሳይ መልኩ ይህንኑ የሕገ መንግስቱን ድንጋጌ እና የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 2(5) በመከተል የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 6 ይዘት “እንደገና አይከሰስም” ብቻ ሳይሆን “እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም” በሚል መስተካከሉ ተገቢ ነው። |
| 2. | አንቀጽ ፯ ስለመያዝና ማሰር<br>ማንኛውም ሰው ወንጀል ስለመፈጸሙ በቂ ጥርጣሬ ሳይኖር ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡ | ድንጋጌው በዚህ መልኩ ሊስተካከል ይገባል፣<br>አንቀጽ ፯ ስለመያዝና ማሰር<br>፩. ማንኛውም ሰው ወንጀል ስለመፈጸሙ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሳይኖር እና መያዙ ለወንጀል ምርመራ ወይም ለፍርድ ሂደቱ የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በቀር ሊያዝ አይችልም፣ ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም።<br>፪. ማንኛውም የታሰረ ሰው በተጠረጠረበት ወይም በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝ ሊጣልበት የሚችለውን የመጨረሻውን የእስር ቅጣት እርከን ያህል በእስር የቆየ እንደሆነ፣ ያለምንም ቅደመ ሁኔታ ሊለቀቅ ይገባል። | ንዑስ አንቀፅ ፩ን በተመለከተ “reasonable suspicion” ለሚለው የኢንግሊዝኛ አገላለፅ ትክክለኛው ትርጓሜ “በቂ ጥርጣሬ” ሳይሆን “ምክኒያታዊ ጥርጣሬ” ነው። “በቂ” የሚለው መለኪያ ከሰው ሰው የሚለያይ (subjective) ሲሆን “ምክኒያታዊነት” የተሻለ objective መለኪያ ነው። በመሆኑም ይህንን አንቀፅ ጨምሮ በ ፳፫፣ ፹፰ ፣ ፻፱ እና ፻፲፫ “በቂ ጥርጣሬ” በሚል የተገለፁት “ምክንያታዊ ጥርጣሬ” በሚል እንዲስተካከሉ አስፈላጊ ነው።<br>በንዑስ አንቀፅ ፪ የተመለከተው ድንጋጌ መጨመር ኢትዮጵያ ፈርማ በተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 9 መሠረት የተ.መ.ድ. ሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ የተያዙ ሰዎችን መብት በተመለከተ በሰጠው አጠቃላይ አስተያየት (General Comment) 35 ላይ የተመለከተውን ምክረ ሃሳብ ለማስፈፀም ያስችላል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | <u>**ለሕገ-ወጥ መያዝና እስር ካሳ ስለመክፈል**</u><br><br>ከዚህ በላይ ከተመለከተው ማሻሻያ በተጨማሪም ለሕገ-ወጥ መያዝ ወይም እስር የተዳረገ ሰው ካሳ የሚያገኝበት ሥነ ሥርዓት አግባብነት ባለው የረቂቅ ሕጉ ክፍል መደንገግ አስፈላጊ ነው። | ምንም እንኳ በረቂቅ ሕጉ ምዕራፍ አራት ላይ አለአግባብ የተሰጠ ፍርድ እንደገና ታይቶ ስህተት ሆኖ ሲገኝ ካሳ የሚከፈልበትን ሥርዓት ያስቀመጠ ቢሆንም ለሕገ ወጥ መያዝና እስር ካሳ ሊከፈለበት የሚያስችልበት ሥርዓት አልተካተተም። ከላይ በተጠቀሰው የተ.መ.ድ. ሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ አጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 35 መሠረት ለሕገ-ወጥ መያዝ ወይም እስር የተዳረጉ ሰዎች ካሳ የሚያገኙበት ሥርዓት መደንገግ ይኖርበታል። ይህም ሕገ-ወጥ እስርን ለመከላከል የሚረዳ ሲሆን አለአግባብ የተበደለ ሰውን በመካስም ፍትሕን የሚያስተካክል ነው፡፡ ቢያንስ መሰረታዊ መርሁ በሥነ ሥርዓት ሕጉ ተደንግጎ ዝርዝር አፈጻጸሙ ወደፊት በሚወጣ ሕግ ሊወሰን ይችላል፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3. | <u>አንቀጽ ፱ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ</u><br><br>በወንጀል የተጠረጠረ፣ የተከሰሰ፣የተፈረደበት ወይም በፍርድ ሂደቱ ተሳታፊ በሆነ ሰው ላይ ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብዓዊ የሆነ ወይም ክብሩን የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡ | አንቀጽ ፱ በሚከተለው መልኩ ሊስተካከል ይገባል፤<br><br><u>አንቀጽ ፱ ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ እና የማሰቃየት ተግባር ስለመከልከሉ</u><br><br>"በማንኛውም በወንጀል የተጠረጠረ፣ የተከሰሰ፣የተፈረደበት ወይም በፍርድ ሂደት ላይ በሆነ ሰው ላይ **የማሰቃየት ተግባር** ወይም ጭካኔ የተሞላበት፣ ኢ-ሰብዓዊና ክብረ ነክ ወይም የሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡" | ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (አንቀፅ 5) እና አለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች ቃልኪዳን (አንቀፅ 7) እንዲሁም ኢሰብዓዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት ለማስቀረት በወጣው ቃል ኪዳን መሠረት በእንግሊዝኛው **torture** የሚባለውን በቀጥታ የሚወክል "የማሰቃየት ተግባር" የሚል አገላለፅ መኖሩ አስፈላጊ ነው።፡ |
| 4. | <u>አንቀጽ ፲፩ ቀልጣፋ ውሳኔ ስለመስጠት</u><br><br>ማንኛውም የምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሂደት በዚህ ሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ይከናወናል፡፡ | ድንጋጌው ሁለት ንዑስ አንቀፆች እንዲኖረው ሆኖ በሚከተለው መልኩ ሊስተካከል፤<br><u>አንቀጽ ፲፩ ቀልጣፋ ውሳኔ ስለመስጠት</u><br><br>፩. ማንኛውም በወንጀል የተጠረጠረ ወይም የተከሰሰ ሰው የተፋጠነ ውሳኔ ወይም ዳኝነት የማግኘት መብት አለው።<br>፪. ማንኛውም የምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሂደት በዚህ ሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥና ከሚያስፈልገው በላይ ሳይዘገይ ይከናወናል። | በመጀመሪያ የተፋጠነ ዳኝነት ማግኘት ሰብአዊ መብት እንደመሆኑ የተጠርጣሪው ወይም የተከሳሹ መብት ሆኖ መደንገጉ ተገቢ ነው። ሌላው ድንጋጌው "የምርመራ፣ የክስና የፍርድ ሂደት በዚህ ሕግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ይከናወናል" ከማለት ባለፈ "ከሚያስፈልገው በላይ ሳይዘገይ" መከናወን ይኖርበታል። ይህ መሆኑ ኢትዮጵያ ፈርማ በተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን በአንቀጽ 14 (3) (ሐ) የተመለከተውን አላግባብ ያልዘገየ ዳኝነት የማግኘት መብት (right to be tried without undue delay) በተሟላ ሁኔታ ጥበቃ እንዲደረግለት ያስችላል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5. | <u>አንቀጽ ፲፪ በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት</u><br><br>፩. ማንኛውም ክስ በግልጽ ችሎት ይታያል፤ ይሰማል፡፡<br>፪. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በተከሳሹና በተጎጂው የግል ሕይወት፣ በሕዝብ የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱ ደኅንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡ | በግልጽ ችሎት ስለመዳኘት የሚለው ርዕስ **"ፍትሃዊ ዳኝነት ስለማግኘት"** የሚል ተጨምሮበት ድንጋጌው በሚከተለው መልኩ ተብራርቶ ሊስተካከል ይገባል፤<br><u>አንቀጽ ፲፪ በግልጽ ችሎት ስለመዳኘትና ፍትሃዊ ዳኝነት ስለማግኘት</u><br><br>፩ ማንኛውም ክስ በህግ በተቋቋመ፣ ስልጣን ባለው፣ ነጻ፣ ገለልተኛ፣ አድልኦ በሌለበትና ግልጽ በሆነ ችሎት (ፍርድ ቤት) ይታያል፡:<br>፪፡ "በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የተከሳሹን ወይም የተጎጂውን የግል ሕይወት የሚጎዳ ሲሆን ወይም በዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ የሕዝብን መልካም ሥነ ምግባር እና ብሔራዊ ደሕንነትን ለመጠበቅ የግድ አስፈላጊ ነው ሲባል ብቻ ጉዳዩ በዝግ ችሎት ሊታይ ይችላል።" | ርዕሱ "ፍትሃዊ ዳኝነት ስለማግኘት" በሚል ጭምር መስተካከሉ ከግልፅ ችሎት በተጨማሪ ያሉትን ሌሎች ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብት (right to fair trial) አካል የሆኑ ጉዳዮችን ለማካተት ያስችላል።<br>ምንም እንኳ በረቂቅ ህጉ አንቀጽ 16 ላይ ስለህጋዊነት መርሆዎች የተደነገገ ቢሆንም ድንጋጌው በዚህ መልኩ ቢስተካከል ኢትዮጵያ ፈርማ ያጸደቀችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን በአንቀጽ 14 (1) ፍትሃዊ የዳኝነት ሥርዓት ሊያሟላ የሚገባቸውን መሰረታዊ መለኪያዎች የሚያሟላ ይሆናል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6. | <u>አንቀጽ ፲፱ የፖሊስ ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት</u><br><br>የፖሊስ ተቋም የወንጀል ምርመራን አስመልክቶ ከዐቃቤ ሕግ የሚሰጠው ትእዛዝ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሕግ መሠረት፤<br>፰. በምርመራ ወቅት በማቆያ ቤት የሚቆዩ ተጠርጣሪዎች አያያዝ ሰብዓዊ ክብራቸውን እና መብታቸውን የጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ግዴታውን ለመወጣት በሚያስችለው መልኩ ያደራጃል፡፡ | የፖሊስ ተቋም ተጠርጣሪዎች በማቆያ ቦታ ለሚደርስባቸው ኢሰብዓዊ አያያዝ ቅሬታ የሚያቀርቡበትን አፋጣኝ፣ አድሎአዊ ያልሆነ፣ግልጽና ተደራሽ የተጠያቂነት ስርዓት የመዘርጋት ኃላፊነት እንዳለበት የሚገልፅ አዲስ ንዑስ አንቀፅ ሊጨመር ይገባል።<br>ይህ ሥርዓት ቅሬታ አቅራቢው ወይም ምስክሮች ከሚያቀርቡት መረጃ ጋር በተያያዘ ማንገላታትና ማስፈራራት የማይደርስባቸው መሆኑን ሊያረጋገጥ ይገባል። | በፖሊስ ጣቢያዎችና ማቆያ ቦታዎች የእስረኛ ሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ ዙሪያ ብዙ ቅሬታዎች የሚነሱ በመሆኑ ተጠርጣሪዎች ወይም ተከሳሾች የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የፈፀሙ አካላት ላይ ቅሬታ የማቅረቢያ እና የተጠያቂነት ሥርዓት መቀመጡ የተያዙ ሰዎችን ሰብአዊ መብቶች ለማስጠበቅ ያስችላል። |
| 7. | <u>አንቀፅ ፳፪ የማረሚያ ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u><br>ማረሚያ ቤት፡....<br>(2) ተጠርጣሪ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ከሕግ አማካሪው፣ ከሐኪሙ ወይም ከኃይማኖት አባቱ የጥብቅና፣ የጤና ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት ለማግኘት እንዲሁም ከጓደኛው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ፣ከትዳር አጋሩ ጋር በግል የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ | የድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 2 በሚከተለው መልኩ ሊስተካከል ይገባል፡፡<br>(2) ተጠርጣሪ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ ከሕግ አማካሪው፣ ከሐኪሙ ወይም ከኃይማኖት መሪው፤ የጥብቅና፣ የጤና ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት ለማግኘት እንዲሁም ከጓደኛው ወይም ከቅርብ ዘመዶቹ ፣ከልጆቹና ከትዳር አጋሩ ጋር በግል የሚገናኝበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡<br>የኃይማኖት አባት የሚለውን የኃይማኖት መሪ በሚል ሊስተካከል ይገባል። | ለልጆች ውጤታማነት የወላጆቻቸው ድርሻ ትልቅ መሆኑ የሚታመን ስለሆነ ምንም እንኳን በወንጀል ተጠርጥረው የታሰሩ ወይም የተከሰሱ ሰዎች ቢሆኑም ልጆችን ጨምሮ ከቤተሰቦቻቸው ጋር በህግ አግባብ በተመቻቸና በተደራጀ መልኩ የሚጎበኙበት ሁኔታ ሊኖር ይገባል፡፡ ይህ መሆኑ ወላጆች የልጆቻቸውን ሁኔታ በቅርበት ለማወቅ የሚያስችላቸው ሲሆን በሌላ መልኩ በልጆች ላይ ሊደርስባቸው የሚችለውን የስነልቦና ጫና በመቀነስ መልካም የቤተሰብ ግንኙነት ለማስቀጠል ያስችላል። በዚህም በሕገ መንግስቱ 36/1/ሐ/ የተደነገገውን ልጆች ያላቸውን የቤተሰብ እንክብካቤን የማግኘት መብት እና |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | (5) በማረፊያ ወይም ማረሚያ ቤት የሚቆዩ ሰዎችን አያያዝ ሰብዓዊ መብታቸውንና ክብራቸውን የጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ | ከንዑስ አንቀጽ 5 በተጨማሪ ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ውስጥ ለሚደርስባቸው ኢሰብዓዊ አያያዝ ቅሬታ የሚያቀርቡበትን አፋጣኝ፣ አድሎአዊ ያልሆነ፣ግልጽና ተደራሽ የሆነ የተጠያቂነት ሥርዓት እንደሚዘረጋ የሚገልፅ አዲስ ንዑስ አንቀፅ (6) ቢታከልበት።<br><br>ይህ ሥርዓት ቅሬታ አቅራቢው ወይም ምስክሮች ከሚያቀርቡት መረጃ ጋር በተያያዘ ማንገላታትና ማስፈራራት የማይደርስባቸው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል። | በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ የተቀመጠውን የወላጆች ግዴታ እንዲሁም የልጆችን መብቶችን ማስጠበቅ የሚቻልበት መንገድ ይፈጥራል፡፡<br>በማረሚያ ቤት የሚገኙ እስረኞች ሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ ዙሪያ ብዙ ቅሬታዎች የሚነሱ እንደመሆኑ የሰብአዊ መብት ጥሰት የተፈፀመባቸው እስረኞች ጥሰት የፈፀሙ አካላት ላይ ቅሬታ የማቅረቢያ እና የተጠያቂነት ሥርዓት መቀመጡ የእስረኞችን ሰብአዊ መብቶች በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ ያስችላል።<br>'የኃይማኖት መሪ' የሚለው አገላለጽ የጾታ ልዩነትን የማያደርግ በመሆኑ በምክረ ሃሳቡ መሰረት ሊስተካከል ይገባል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8. | <u>አንቀጽ ፳፮ የወንጀል ምርመራ</u><br><br>፪. የወንጀል ምርመራ መረጃ እና ማስረጃን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ | ንዑስ አንቀፅ ፪ በሚከተለው መልኩ ሊስተካከል ይገባል፡<br><br>“የወንጀል ምርመራ ማስረጃን መሠረት ያደረገ መሆን ይኖርበታል።” | “መረጃ እና ማስረጃ” የሚለው አገላለፅ በኢትዮጵያ ከቅርብ ግዜ ወዲህ እየተለመደ የመጣ አገላለጽ ቢሆንም በሕግ እይታ አላስፈላጊ ወይም ትርጉም አልባ ነው። “ማስረጃ” የሚለው ቃል (ፅንሰ ሃሳብ) በራሱ ሰፊና “መረጃ”ን የሚያጠቃልል እንደመሆኑ በቂ ነው። |
| 9. | <u>አንቀጽ ፳፯ በምርመራ ወቅት ተመጣጣኝ ኃይል ስለመጠቀም</u><br><br>፩. መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪን ለመያዝ ፣ለብርበራ እና በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ተመጣጣኝ ኃይል ሊጠቀም ይችላል፡፡<br><br>፪. መርማሪ ፖሊስ የምርመራ ተግባሩን ለማከናወን የሚጠቀምው ተመጣጣኝ ኃይል የግድ አስፈላጊ ሲሆንና ሌላ አማራጭ መንገድ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። | ርዕሱ፡ “ስለ ሃይል አጠቃቀም” በሚል ተቀይሮ ድንጋጌው እንደሚከተለው ተብራርቶ ሊስተካከል ይገባል፤<br><br><u>አንቀጽ ፳፯ ስለ ኃይል አጠቃቀም</u><br><br>“መርማሪ ፖሊስ ተጠርጣሪን ለመያዝ፣ ለብርበራ እና በልዩ የወንጀል ምርመራ ዘዴ ኃይል ሊጠቀም የሚችለው ጥንቃቄ የማድረግ፣ የህጋዊነት፣ የጥብቅ አስፈላጊነት፣ የተመጣጣኝነት እንዲሁም አድልኦ ያለማድረግ መርሆችን ባከበረ መልኩ እና ሌላ አማራጭ መንገድ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።” | በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት ማዕቀፍ የወጡ ተገቢነት ያላቸው መመርያዎች የኃይል አጠቃቀም ከተመጣጣኝነት መርህ አንጻር ሊያሟላቸው የሚገባቸውን መስፈርቶች ያስቀምጣሉ። በነዚህ መመርያዎች መሠረት የኃይል አጠቃቀም የሚገዛባቸው ዋና መርሆች፡ ጥንቃቄ የማድረግ መርህ (principle of precaution)፣ የሕጋዊነት መርህ (principle of legality)፣ የጥብቅ አስፈላጊነት መርህ (principle of necessity)፣ የተመጣጣኝነት መርህ (principle of proportionality) እና አድልኦ ያለማድረግ መርህ (principle of non-discrimination) ናቸው።<br>በዚህ ረገድ ተጠቃሽ የሆኑት መመርያዎች፡ Code of Conduct for Law Enforcement Officials እና Basic Principles on the Use of Force and Firearms by Law Enforcement Officials ናቸው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10. | <u>አንቀጽ ፹ የምስክር ቃል መቀበል</u><br><br>፩. መርማሪ ፖሊስ በምርመራ ክፍል ወይም ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ የምስክሮችን ቃል ይቀበላል፡፡<br><br>፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም በሕመም፣ በዕድሜ ወይም በሌላ አስገዳጅ ምክንያት የምስክሩን ቃል በምርመራ ክፍል መቀበል የማይቻል እንደሆነ ምስክሩ በሚገኝበት ወይም አመቺ በሆነ ቦታ የምስክርነት ቃሉን መቀበል ይቻላል፡፡<br>፫. መርማሪው ምስክሩ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ፡-<br><br>(ሀ) የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በወንጀል የሚያስከስሰው ከሆነ ለመመስከር እንደማይገደድ፣ ቃሉን ለመስጠት ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ እንደሆነ እና የሚያውቀውን እንዲናገር፣ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት አስፈላጊውን ጥበቃ እንደሚደረግለት ለምስክሩ መንገር፤<br>(ለ) የአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተፈፀመበት ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ በተለይም በወንጀል ድርጊት ተጎጂ የሆነ ሰው የምስክርነት ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚቱ ወይም አሳዳሪው እና የማኅበራዊና የሥነልቦና ምክርና ድጋፍ የሚሰጥ ባለሙያ መገኘቱን ማረጋገጥና ለምስክሩ ማስተዋወቅ፤ ይኖርበታል፡፡<br>፬.የምስክርነት ቃል አቀባበል፡-<br><br>(ሀ) ከመርማሪ ለሚቀርብ ጥያቄ በቃል ፣ በምልክት ወይም እንደምስክሩ ሁኔታ አመቺ በሆነ መንገድ ምላሽ በመስጠት ይመዘገባል፡፡ | የማሻሻያ ምክረ ሃሳቦች<br>- በንዑስ አንቀፅ ፪ በተዘረዘሩት ውስጥ "ምስክርነት በመስጠት ምክንያት ለመልሶ ማጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች፤ መንቀሳቀስን ከሚገድብ የአካል ጉዳት ጋር አብረው የሚኖሩ ሰዎች" የሚል እንዲጨመርበት፤<br><br>-በአንቀጽ 80(3)(ለ) የምስክርነት ቃል በመስጠት ወቅት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል የተባሉት ሰዎች መካከል **የጾታዊ ጥቃት ተጎጂዎች** ተብሎ እንዲጨመር፤<br><br>-በንዑስ አንቀፅ 4 ሥር ከተዘረዘሩት መካከል የሚከተሉት የንዑስ ንዑስ አንቀፆች (መ እና ሠ) እንዲጨመሩ፤<br><br>(መ) ፖሊስ የምስክርነት ቃል በመቀበል ሂደት በምስክሮች ላይ ማንኛውንም አይነት የኃይል ወይም የማስገደድ ድርጊት ወይም ሌላ ተፅዕኖ የሚያደርግ ተግባር መፈፀም የለበትም።<br>(ሠ) ፖሊስ ወይም መርማሪው ጾታን ወይም ሥርዓተ-ጾታን መሠረት ያደረገ ጥቃት ወንጀል የተፈጸመበትን ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ሰውን ቃል በሚቀበልበት ጊዜ ከዚህ በታች የተመለከቱትን መሠረታዊ የቃለመጠይቅ መርሆችን መከተል ይገባዋል፡፡<br>1. በአክብሮት ማነጋገር<br>2. የቃል ሰጪው/ዋን ሰብአዊ ክብር መጠበቅ<br>3. ገለልተኛ መሆኑን ማሳየት<br>4. የፍረጃ ቃላትን አለመጠቀም | የምስክርነት ቃልን ባሉበት ሆኖ ለመስጠት ዕድል ከሚያገኙት ሰዎች ውስጥ ምስክርነት በመስጠት ምክንያት የመልሶ ማጥቃት ችግር የሚገጥማቸው በተለይ የጾታዊ ጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎች መዘንጋት የለባቸውም። ለብዙዎቹ የጥቃት ሰለባዎች ወደፍትህ አካላት አለመሄድ ወይም ከሄዱ በኃላ መቅረትና ጉዳይን ማቋረጥ አንዱ ምክንያት በአጥቂው የመልሶ መጠቃት ዕድል ከፍተኛ መሆኑ ነው። በሌላ በኩል የአካል ጉዳት ላለባቸው ሰዎች የፍትህ አካላት ተደራሽ አለመሆን ካሉበት ቦታ ርቀትና አቀማመጥ አንጻር የሚነሳ ነው። ምክረ ሃሳቡ በጾታዊ ጥቃት በተለይ የቤት ውስጥ ጥቃት፤ ወሲባዊ ትንኮሳ የመሳሰሉ ጥቃቶች ተጎጂዎች/ሰለባዎች በከፍተኛ የስነልቦና ጫና ውስጥ የሚገኙ ሰዎች መሆናቸውን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ነው፡፡እነዚህ ጥቃቶች ከአስገድዶ መድፈር ባልተናነሰ ሁኔታ ሴቶችንና ሕፃናትን በከፍተኛ የስነልቦና ችግር ውስጥ የሚያስገቡ ናቸው።<br>ምንም እንኳን በአንቀፅ 80 (3) (ሀ) ስር መርማሪው ምስክሩ ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የሚሰጠው የምስክርነት ቃል በወንጀል የሚያስከስሰው ከሆነ ለመመስከር እንደማይገደድ፣ ቃሉን ለመስጠት ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ እንደሆነ የመግለፅ ኃላፊነት እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም ከመናገር ባለፈ በምስክሩ ላይ ማንኛውም የኃይል ወይም የማስገደድ ድርጊት ወይም ሌላ ተፅዕኖ የሚያደርግ ተግባር መፈፀምን የሚከለክል ግልጽ ድንጋጌ መኖሩ ለምስክሮች ተጨባጭ ዋስትና የሚሰጥ ነው።<br>መርማሪው የምስክርነት ቃል ሲቀበል ሊከተላቸው የሚገቡ መርሆችን መዘርዘር ፈራጅ የሆኑ ቃላትን እንዳይናገር፤ ምስክሩን በአክብሮት እንዲያነጋግር፤ ወዘተ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡ እነዚህ ክልከላዎች በሌሉበት ሁኔታ በምስክርነት የሚቀርቡ ሰዎች በተለይም የወንጀል ድርጊቱ ተጠቂ የሆኑ ሰዎች በሚደርስባቸው እንግልት የተነሳ በጉዳያቸው ሳይገፉበት ሲቀሩ ይታያል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | (ለ) ጥያቄና መልሱን ጥያቄው በቀረበበትና ምስክሩም በመለሰበት አግባብ በመመዝገብ፣ እንደ አስፈላጊነቱም ሂደቱን በምስል ወይም በድምጽ በመቅረጽ ሊከናዎን ይችላል፡፡ የምስክርነት ቃል መስጠት ሲጀመርና ሲጠናቀቅ ስለሂደቱ የምስክሩ ማንነት፣ አድራሻና ቃሉን በፈቃደኝነት ስለመስጠቱ ይመዘግባል፡፡<br><br>(ሐ) የተመዘገበውን የምስክርነት ቃል ለምስክሩ ተነቦለት በየገጹ እንዲፈረም ይደረጋል፡፡ ሆኖም ምስክሩ ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ይኸው ይመዘገባል፡፡ | 5. በጉዳዩ ላይ ውጤታማ ምርመራ ለማካሄድ የግድ አስፈላጊ መሆኑ ካልታመነበት በስተቀር መሪ ጥያቄዎችን ከማቅረብ መቆጠብ<br>6. ሀሳብን ሙሉ በሙሉ ለመግለጽ የሚያስችሉ ክፍት ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡ | |
| 11. | <u>አንቀጽ ፹፬ የተያዘን ሰው ስለመበርበር</u><br>፩. የተያዘ ሰው የሚበረበረው ተመሳሳይ ፆታ ባለው ሰው ሲሆን፣ ብርበራውም አካላዊ ጤንነቱንና ደህንነቱን በማይጎዳ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ | የድንጋጌው ንዑስ አንቀጽ 1 ከዚህ በታች እንደተመለከተው ተብራርቶ ሊስተካከል ይገባል፤<br><u>አንቀጽ ፹፬ የተያዘን ሰው ስለመበርበር</u><br>፩. የተያዘ ሰው የሚበረበረው ተመሳሳይ ፆታ ባለው ሰው ሲሆን፣ ብርበራውም የተጠርጣሪውን አካላዊ ጤንነቱን፣ ደህንነቱንና ሰብአዊ ክብሩን በማይጎዳ መልኩ ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡ | በዚህ መልኩ ድንጋጌው መስተካከሉ ብርበራ ከአካላዊ ጤንነትና ደህንነት መብቶች በተጨማሪ ሌሎች ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ መልኩ እንዲከናወን ያስችላል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 12. | <u>አንቀጽ ፺፫ ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ መገኘት</u><br>፪. መርማሪው ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ እንደደረሰ፡-<br>(ሀ) በቦታው የወንጀል ተጎጂ ወይም የሞተ ሰው መኖሩን ያረጋግጣል፤ የወንጀል ተጎጂ ካለ እንደ አስፈላጊነቱ ተገቢው የሕክምና ርዳታ እንዲያገኝ፣ የሞተ ሰው ካለ ምርመራ እንዲደረግ ወደ ሕክምና ተቋም እንዲደርስ ያደርጋል፡፡ | መርማሪው ወንጀል በተፈጸመበት ሥፍራ እንደደረሰ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ የደህንነት ጥበቃ/የሕግ ከለላ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች/ተጠቂዎች ጥበቃ የሚያገኙበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ ሊጨመር ያስፈልጋል። | በተጠቀሰው አንቀጽ መርማሪው ወንጀል በተፈጸመበት ቦታ እንደደረሰ ማድረግ ስላለበት ነገሮች የተጠቀሰ ሲሆን ስለሕክምና ወዘተ ቢጠቅስም የደህንነት ጥበቃ የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች ጥበቃ እንዲያገኙ ስለማድረግ ምንም አለማለቱ ሰፊ ክፍተት ሲሆን በተለይ በጾታዊ ጥቃት የተጠቁ ሰዎችን ሁኔታ ከግምት ያላስገባ በመሆኑ ሊስተካከል ይገባል ፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 13. | ክፍል አምስት ልዩ የወንጀል የምርመራ ዘዴዎች<br><br>አንቀጽ ፻፩ ዓላማ<br><br>የልዩ ወንጀል ምርመራ ዘዴ ዓላማ በመደበኛው የምርመራ ዘዴ ማስረጃ ማሰባሰብ ባልተቻለበት የሙስና የወንጀል፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል እና የሽብር ወንጀል ጉዳዮች ላይ ማስረጃ ለማሰባሰብ **ወይም ይህን የምርመራ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡**<br>አንቀጽ ፻፬ መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች<br><br>፫. ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ፤<br>(ሀ) የሚታወቅ ከሆነ የተጠርጣሪውን ስምና አድራሻ፣<br>(ለ) እንደነገሩ ሁኔታ ትእዛዙ የሚፈጸምበት ቦታ ወይም አድራሻ፣<br>(ሐ) ትእዛዙ ተፈጻሚ የሚሆንበት የጊዜ ገደብ፣<br>(መ) በልዩ ወንጀል ምርመራ ዘዴ የሚሰበሰበውን ማስረጃ፣ እና<br>(ሠ) ሌላ አግባብነት ያለውን ዝርዝር መረጃ መያዝ፤ ይኖርበታል፡፡ | የማሻሻያ ምክረ ሃሳቦች<br>አንቀፅ 101 ስር “**ወይም ይህን የምርመራ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ**” የሚለው ሃረግ ሊወጣ ይገባል፤<br>ልዩ ምርመራ ዘዴ ጥቅም ላይ ከሚውልባቸው የወንጀል አይነቶች መካከል **በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች** (በተለይ እንደ አስገድዶ መድፈር እና ወሲባዊ ትንኮሳ ያሉና ማስረጃ የማግኘት ችግር የሚገጥማቸው ጉዳዮች) ሊካተቱ ይገባል።)<br>በአንቀፅ 104 ንዑስ አንቀጽ 3 (ሀ) ስር “የሚታወቅ ከሆነ” እንዲሁም በፊደል (ለ) ስር “እንደነገሩ ሁኔታ” የሚሉት ሃረጎች ሊሰረዙ ይገባል፣<br>በክፍል አምስት የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ሊካተት ይገባል፣<br>“ዐቃቤ ሕግ የልዩ ወንጀል ምርመራ ዘዴዎች ተግባራዊ አፈጻጸም ሰብዓዊ መብቶችን ባከበረ መልኩ መሆኑን በቅርብ ይከታተላል፣ ይህን በጣሱ ሰዎች ወይም አካላት ላይ የወንጀል ክስን ጨምሮ ሌሎች አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች ይወስዳል፣ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የቅሬታ ማቅረቢያ ሥርዓት ይዘረጋል።” | ልዩ የምርመራ ዘዴዎች በሰብዓዊ መብቶች ላይ የተለየ ጫና የሚፈጥሩ እንደመሆናቸው እና በመደበኛነት ጥቅም ላይ ሊውሉ የማይገባቸው በመሆኑ ተፈፃሚ የሚሆኑባቸው ወንጀሎች በግልፅ ተለይተው ሊቀመጡ ይገባል።<br>“**ይህን የምርመራ ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ**” የሚለው የተለጠጠ ሃረግ ልዩ የምርመራ ዘዴዎች በሰፊው ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉበትን ሁኔታ በመፍጠር የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አደጋን የሚፈጥር ነው። ልዩ የምርመራ ዘዴዎች ተፈፃሚ የሚሆኑባቸው የወንጀል አይነቶች ወይም ሁኔታዎች በሕግ አውጭው በግልፅ መቀመጥ ይኖርባቸዋል።<br>ሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጾታዊ ጥቃቶችን በተመለከተ በተደጋጋሚ ከሚገጥሙት ዋነኛ ተግዳሮቶች አንዱ ጥቃቱ ብዙ ጊዜ በድብቅ የሚፈጸም በመሆኑ ማስረጃ የማጣት ሁኔታ ነው፡፡ እንደ አስገድዶ መድፈር ላሉ ሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን መጠቀም ይህንን ከማስረጃ ጋር የተያያዘ ችግር በመቅረፍ ለሴቶች መብቶች መከበር የጎላ አስተዋፆ ሊያደርግ ይችላል።<br>የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች የኮሚሽነሩ ቢሮ (UN Office of the High Commissioner for Human Rights) እ.አ.አ. በ 2014 ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ (UN General Assembly) ባቀረበው ሪፖርት (A/HRC/27/37) የልዩ ምርመራ ዘዴ በሲቪልና ፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን አንቀጽ 17 ላይ የተመለከተውን የግል ሕይወት፣ቤተሰብ፣ መኖሪያ ቤት ወይም የመረጃ ልውውጥ (communication) ያለ አግባብ ወይም ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ያለመደፈር መብትን ሊጎዳ እንደሚችልና መወሰድ ስላለባቸው ዝርዝር የጥንቃቄ እርምጃዎች ያመላክታል። ከነዚህ እርምጃዎች አንዱ የሆነው **የምርመራ ዘዴው ጥቅም ላይ የሚውልባቸውን ሰዎችንና ሁኔታዎች** የሃገራት ህጎች በግልጽ ሊያመላክቱ እንደሚገባ የተሰጠው ምክረ ሃሳብ ሲሆን በተያያዥ **በጅምላ የሚደረግ መረጃ ማሰባሰብ አግባብነት እንደሌለው ይገልጻል**። ከዚህ በተጨማሪ ሃገራት ልዩ የምርመራ ዘዴዎችን አፈጻጸም በየጊዜው ሊመረምሩና ለሕገ ወጥ ዓላማ ውሎ ከተገኘም ተጠያቂነትን ሊያስከትል የሚችል ሥነ-ሥርዓት በሕግ ሊደነግጉ እንደሚገባ ያሳስባል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 14. | <u>አንቀጽ ፻፲፪ በእጅ ከፍንጅ ወንጀል ተጠርጣሪን መያዝ</u><br><br>፩. ማንኛውም ሰው ወይም ፖሊስ ከሦስት ወር በማያንስ ቀላል እሥራት የሚያስቀጣ የእጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈፅም የተገኘን ተጠርጣሪ ያለ ፍርድ ቤት የመያዣ ትእዛዝ መያዝ ይችላል፤<br>፪ በግል አቤቱታ የሚያስቀጣ ወንጀል እጅ ከፍንጅ ሲፈጽም የተገኘ ተጠርጣሪ በፖሊስ ሊያዝ የሚችለው በግል ተበዳይ አቤቱታ ሲቀርብ ብቻ ነው፡፡ | የማሻሻያ ምክረ ሃሳቦች፡-<br>በንዑስ አንቀፅ ፩ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠርጣሪው የተያዘው የፖሊስ አባል ባልሆነ ሰው እንደሆነ ተጠርጣሪው ወዲያው (በተቻለ ፍጥነት) ለፖሊስ ተላልፎ መሰጠት እንዳለበት የሚገልፅ ተከታይ ድንጋጌ ያስፈልጋል።<br><br>በንዑስ አንቀፅ 2 የተቀመጠው ቢኖርም በግል አቤቱታ የሚያስቀጣው ወንጀል በመፈፀም ላይ ያለ እንደሆነ ፖሊስ የማስቆም ኃላፊነት እንዳለውና ተጠርጣሪው የወንጀል ድርጊቱን የማያቆም እንደሆነ በግል ተበዳይ ስምምነት ላይ በመመስረት ተጠርጣሪውን መያዝ እንደሚችል ይገለፅ፡፡ | የሰዎች መያዝ የአካል ነፃነት እና የመንቃሳቀስ መብታቸውን የሚገድብ እንደመሆኑና የሕግ አስከባሪ ያልሆኑ ግለሰቦች ስለ ሕግ ወይም ወንጀል ስለመፈፀሙ ያላቸው ግንዛቤ የተወሰነ እንደመሆኑ በዚህ መልክ የተያዙ ሰዎች በአስቸኳይ ለፖሊስ እንዲተላለፉ መደረግ አለበት። ይህ መሆኑ የተያዙ ሰዎች በሕገ መንግሥቱ መሠረት በተያዙበት 48 ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብታቸውን ለማረጋገጥ ያስችላል።፡<br>የንዑስ አንቀጽ 2 ማሻሻያ በተለይ በሴቶች እና ለመብት ጥሰት ተጋላጭ በሆኑ ሰዎች ላይ የሚደረጉ የትንኮሳ ድርጊቶችን ለመከላከል ጠቃሚ ነው። |
| 15. | <u>አንቀጽ ፻፲ ተጠርጣሪ ሲያዝ ስለሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት</u><br>፫ ተጠርጣሪው በቃል ወይም እጁን በመስጠት እንዲያዝ ያልተስማማ እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ ሰውነቱን በመንካት ወይም በመጨበጥ መያዝ ይችላል፡፡<br><br>፬ ተጠርጣሪ ላለመያዝ በኃይል የተከላከለ ወይም ለማምለጥ የሞከረ እንደሆነ መርማሪ ፖሊስ ሁኔታው የሚፈቅደውን ተጠርጣሪውን ለመያዝ የሚያስችል ተመጣጣኝ ኃይል በመጠቀም ለመያዝ ይችላል፡፡ | ንዑስ አንቀፅ ፫ እና ፬ ወደ አንድ ተጨምቀው ከታች በተመለከተው መልኩ ሊስተካከል ይገባል፡-<br>"ተጠርጣሪው ህግን መሰረት ያደረገ መያዝን በኃይል የተከላከለ እንደሆነ፣ ፖሊስ ጥንቃቄ የማድረግ፣ የህጋዊነት፣ የጥብቅ አስፈላጊነት፣የተመጣጣኝነት እንዲሁም አድልኦ ያለማድረግ መርሆችን ባከበረ መልኩ ሃይል ተጠቅሞ ሊይዘው ይችላል።"<br>ተጠርጣሪ ሲያዝ መደረግ ከሚገባቸው ሥነ-ሥርዓቶች መካከል የሚከተሉት ሊጨመሩ ይገባል፡፡<br>"ተጠርጣሪው በሚያዝበት ጊዜ የተያዘበትን ምክንያት፣ እንዲሁም ያለመናገርና የሚጠየቀውን ጥያቄ ያለመመለስ መብት እንዳለውና እና በነፃ ፈቃዱ የሚሰጠው ማንኛውም ቃል በፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችልና በተጨማሪም ለፖሊስ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ጠበቃ የመጥራት እና ቃሉን በሚሰጥበት ግዜ ጠበቃው እንዲገኝ የማድረግ መብት እንዳለው በሚረዳው ቋንቋ ወዲያውኑ ሊነገረው ይገባል።" | ከላይ በተራ ቁጥር 9 ስለ ሃይል አጠቃቀም የተመለከቱት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕግጋት ማዕቀፍ ተፈጻሚነት ያላቸውን መርሆች በህጉ እንዲካተቱ ያስችላል።<br>ምንም እንኳን ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ያለመናገር መብት እንዳለውና በፈቃደኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል ሊነገረው እንደሚገባ በአንቀፅ ፻፲፯ (፪) የተገለፀ ቢሆንም በሚከተሉት ምክንያቶች ይህ ጉዳይ በአንቀፅ ፻፲፯ (የተጠርጣሪነት ቃል) ሳይሆን በአንቀፅ ፻፲ ሥር በተስተካከለው መሠረት ሊደነገግ ይገባል።<br>1. የዳበረ የፍትሕ ሥርዓት ያላቸው የተለያዩ ሃገሮች ልምዶች እንደሚያሳየው ያለመናገር መብት እንዳለውና በፈቃደኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል ሊነገረው የሚገባው በተያዘበት (አካላዊ ነፃነቱ ወይም የመንቀሳቀስ መብቱ በተገደበበት) ቅፅበት ነው። በመሆኑም ይህ ጉዳይ ተጠርጣሪ ሲያዝ ስለሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት የሚደነግገውን አንቀፅ ፻፲ ብሎም የተጠርጣሪውን የጣት አሻራ፣ ፎቶግራፍና ናሙና ስለመውሰድ የሚናገረውን አንቀጽ ፻፲፮ አልፎ የተጠርጣሪነት ቃል ስለመስጠት በሚናገረው አንቀፅ ፻፲፯ መካተቱ ተጠርጣሪው መብቶቹ የሚገለፁለት ከተያዘና የጣት አሻራ፣ ፎቶግራፍና ናሙና ከሰጠ በኃላ ዘግይቶ እንደሆነ አይነት ስዕል ይሰጣል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | “ፖሊስ ወይም ተጠርጣሪውን የያዘው አካል ይህን ግዴታ መፈጸሙን ማረጋገጥ ካልቻለ በዚህ ሁኔታ የተሰበሰበው ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም።”<br>“የተያዘው ሰው የአይምሮ ህመም ያለበት እንደሆነ ለወላጆቹ፣ ለቤተሰቡ፣ ለአሳዳጊው፣ ለሞግዚቱ ወይም ለህግ አማካሪው መያዙንና የተያዘበትን ህጋዊ ምክንያት በተቻለ ፍጥነት ሊነገረው ይገባል” | **2.** ተጠርጣሪው ያሉትን መብቶች ወዲያውኑ እንዲያውቅ አለመደረጉ ባለማወቅ ጥፋተኝነቱን እንዲያምን ወይም ሳይጠየቅ ጭምር ራስን የመወንጀል አይነት ውጤት ያለውን ቃል ሊሰጥ የሚችልበትን አደጋ ይፈጥራል።<br>3. ረቂቅ ሕጉ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ሕገ መንግሥት አንቀጽ 19 (2) ተጠርጣሪው ያለመናገር መብት እንዳለውና በፈቃደኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል ሊነገረው እንደሚገባው መገለፁ መልካም ነገር ቢሆንም ሕጉ ከዚህ በተጨማሪ ተጠርጣሪው የተያዘበትን ምክንያት፣ እንዲሁም ለፖሊስ ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ጠበቃ የመጥራት እና ቃሉን በሚሰጥበት ግዜ ጠበቃው እንዲገኝ የማድረግ መብት እንዳለው በሚረዳው ቋንቋ ወዲያውኑ ሊነገረው እንደሚገባ በግልፅ መንደንገጉ ኢትዮጵያ ርፈማ በተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 9 ላይ ስለተያዙ ሰዎች መብቶች የተዘረዘሩ መስፈርቶችን እንዲሁም በአንቀጹ ላይ ዝርዝር ማብራሪያ የሚሰጠውን General Comment 35 ላይ የተመለከቱትን ምክረ ሃሳቦች ለማስፈፀም ያስችላል።<br>የአይምሮ ህመም ያለበት ሰው ሲያዝ ለወላጆቹ፣ ለቤተሰቡ፣ ለአሳዳጊው፣ ለሞግዚቱ ወይም ለህግ አማካሪው መያዙንና የተያዘበትን ህጋዊ ምክንያት በተቻለ ፍጥነት ሊነገረው እንደሚገባ የተ.መ.ድ. ሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ በሰጠው አጠቃላይ አስተያየት General Comment 35 ይመክራል። |
| 16. | <u>አንቀጽ ፻፲፫ የጣት አሻራ፣ ፎቶግራፍና ናሙና መውሰድ</u><br>፫. ተጠርጣሪው ከሰውነቱ በቀጥታ የሚወሰድ እንደ ደም፣ ሽንት፣ ጸጉር ወይም መሰል ናሙናዎችን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ የተጠረጠረበት ነገር እንደተረጋገጠ እንደሚገመት ይደነግጋል፡፡ | ንዑስ አንቀፅ 3 ሙሉ በሙሉ ከረቂቁ ሊወጣ ይገባል፡፡ | በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት እንዲሁም ኢትዮጵያ በተቃበለቻቸው ዓለም አቀፍ ሕግጋት መሠረት ማንኛውም ሰው ከፍርድ በፊት ንጹህ ሆኖ የመገመት፣ ያለመናገር፣ በራስ ላይ እንዲመሰክር ያለመገደድ እና የግል ሚስጥሩ የመጠበቅ መብቶች አለው። ከፍርድ በፊት ንጹህ ሆኖ የመገመት መብት መሠረታዊ መብት እንደመሆኑ ፖሊስ/ዐቃቤ ሕግ ወንጀል ስለመፈጸሙ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ በላይ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ ወንጀልን የመመርመርና ትክክለኛውን ወንጀለኛ ለይቶ የማውጣትና ለፍትህ የማቅረብ ግዴታ ደግሞ የመንግስት ነው፡፡ ይህንን ለመፈጸም ፖሊስ የመንግስት አካል እንደመሆኑ የሙያ፣ የቴክኖሎጂ እና ሌሎች አስፈላጊ አቅሞች አሉት፡፡ እንዲሁም ተጠርጣሪው ወንጀለኛ ሆኖ ከተገኘ ህይወቱን ወይም ነጻነቱን ጭምር ሊያጣ እንደሚችል ይታወቃል፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ከሌሎች የዳበረ የሕግ ሥርዓት ካላቸው ሃገራት ልምድ ለመረዳት እንደሚቻለው በተጠርጣሪው አለመተባበር ላይ ተመስርቶ የሚወሰድ የሕግ ግምት (adverse inference) በፍትሐ ብሔር ሕግ የተወሰነ ተፈፃሚነት ቢኖረውም፤ የተጠርጣሪውን ከፍርድ በፊት ንጹህ ሆኖ የመገመት፣ ያለመናገር እና በራስ ላይ እንዲመሰክር ያለመገደድ መብቶችን ስለሚፃረር በወንጀል ሕግ ተፈፃሚነት የለውም።<br>ስለሆነም ተጠርጣሪው ናሙናዎቹን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ፖሊስ ሌሎች አማራጭ የምርመራ ዘዴዎችን ተጠቅሞ እውነትን ማውጣት ከሚጠበቅበት በስተቀር ፈቃደኛ አለመሆኑ የተጠረጠረበት ነገር እንደተፈጸመ እንዲቆጠር መደንገጉ አግባብነት የሌለው በመሆኑ ሊሰረዝ ይገባል፡፡ |
| 17. | <u>አንቀጽ ፻፲፯ የተጠርጣሪነት ቃል</u><br><br>፩. በወንጀል ተጠርጥሮ ለምርመራ እንዲቀርብ የተጠራ ወይም ተይዞ የቀረበ ሰው ስሙ፣ ፆታው፣ ዕድሜው፣ ዜግነቱ እና አድራሻው ተረጋግጦ ለቀረበበት የወንጀል ወይም የግል አቤቱታ ቃሉን እንዲሰጥ ይጠየቃል፡፡<br>፪. ተጠርጣሪው ቃሉን ከመስጠቱ በፊት ምላሽ ለመስጠት ነፃ እንደሆነና ያለመናገር መብት እንዳለው፣ በፈቃደኝነት የሚሰጠው ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብበት እንደሚችል መንገር እና ይኸው መከናዎኑ በጽሑፍ መገለጽ ይኖርበታል፡፡<br>፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ተጠርጣሪው ያለመናገር መብት ያለው መሆኑ የተደነገገው ቢኖርም ተጠርጣሪው ስሙን፣ ጾታውን፣ ዕድሜውን፣ ዜግነቱንና አድራሻውን እንዲገልጽ ለሚቀርብለት ጥያቄ ትክክለኛውን ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፡፡<br>፬. ተጠርጣሪው ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኛ እንደሆነ ከመርማሪ ለሚቀርብለት ጥያቄ እንደአግባቡ | በአንቀፅ 116 ሥር ከተደነገጉት መካከል የሚከተሉት ማሻሻያዎች ሊጨመሩ ይገባል፤<br><br>የቃል አቀባበል ሥርዓቱ የተጠርጣሪውን ሰብአዊ መብቶች ባከበረ መንገድ መከናወን እንዳለበት መገለፅ አለበት።<br>ዛቻ፣ ስድብ፣ ማስፈራራት፣ ድብደባ፣ ማሰቃየት፣ የጭካኔ፣ ኢሰብአዊና የሚያዋርድ ተግባር እንዲሁም የተራዘመ ወይም ተደጋጋሚ የቃል አቀባበል ክልከላ መደረግ አለበት።<br>ተጠርጣሪው እጅ ከፍንጅ ወንጀል ሲፈፅም በተገኘበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ቃል የሚሰጠው በቀን (ከንጋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ) እንደሆነ መደንገግ አስፈላጊ ነው፡፡<br>ተጠርጣሪው አካለ መጠን ያልደረሰ ወይም የአዕምሮ ህመም ወይም የአዕምሮ እድገት ውስንነት ያለበት ከሆነ ከወላጆቹ አንዱ ወይም እንደሁኔታው አግባብ ህጋዊ ሞግዚቱ ሳይገኙ ቃሉን ሊሰጥ አይገባም።<br>የሞት ፍርድ ወይም 7 ዓመትና በላይ የእስራት ቅጣት በሚያስከትል ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ጠበቃው ወይም መንግስት የሚመድብለት የመከላከያ ጠበቃ ሳይገኝ ቃሉን እንዲሰጥ የማይገደድ መሆኑን መደንገግ አለበት።<br>ያለመናገር መብት ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የክስ እና ዳኝነት ሂደቱ ተፈፃሚነት | ምንም እንኳ ረቂቅ ህጉ የተያዙና የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብር መጠበቅ እንዳለበት በጠቅላላው የሚደነግግና ይህም በቃል መቀበል ሥርዓት ላይም ተፈጻሚ እንደሆነ ቢታመንም፣ በምክረ ሃሳቡ የተመለከተው ተጨማሪ ድንጋጌ  መካተቱ እና መርማሪው ያለበትን ግዴታ በግልጽ ማመላከቱ ተግባራዊነቱን የበለጠ የሚያጠናክር ከመሆኑም በላይ በቃል አሰጣጥ ሂደት የሚስተዋሉ ክብርን የማዋረድ ድርጊቶችን  በዘላቂነት ለመቅረፍ ያስችላል።<br><br>በምክረ ሃሳቡ የተጠቀሱት ተጋላጭ የማህበረሰብ ክፍሎች ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል በተለየ መልኩ መብቶቻቸውን ለማስጠበቅ (ያለ መናገር መብትን ጨምሮ ሌሎች አካላዊና አዕምሮአዊ ደህነነትን የሚመለከቱ ሁኔታዎች) የሚያስቸግራቸው በመሆኑ ቃል በመስጠት ሂደት ወላጆቻቸው ወይም ሞግዚታቸው  መገኘታቸው ለመብታቸው መከበር ጉልህ አስተዋጽኦ ያደርጋል። በተመሳሳይ መልኩ ሊመለስ በማይችል የወንጀል ቅጣት፣ በተለይም የሞት ቅጣትንና ረዥም የእስር ጊዜን ሊያስከትል በሚችል ወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎች ፍትሃዊ፣ ተአማኒ እና ውጤታማ በሆነ የወንጀል ሥርዓት ለመዳኘት ያስችላል።<br><br>ያለመናገር መብት ፅንሰ ሃሳብ በአለም አቀፍ ሕግም ሆነ በሃገራት ልምድ ለፖሊስ ቃል በመስጠት ሂደት የተወሰነ ሳይሆን ማንኛውም ተከሳሽ በዳኝነት ሂደቱም ጭምር ሊጠቀመው የሚችለው መብት እንደመሆኑ ይሄው በግልፅ መደንገጉ ተገቢ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | በቃል፣ በጽሑፍ፣ በምልክት ወይም በአስተርጓሚ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ቃሉን የሰጠው በአስተርጓሚ ከሆነ አስተርጓሚውም የተጠየቀውንና የሰጠውን ምላሽ ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡<br>፫. ተጠርጣሪው ለሚቀርብለት ጥያቄ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ ሂደቱ በምስል ወይም በድምፅ ሊቀረፅ ይችላል፡፡<br>፬. መርማሪ ተጠርጣሪው የሰጠውን ቃል ብቻ ይመዘግባል፤ ይህንኑም በእርሱና በተጠርጣሪው እንዲፈረም ያደርጋል፤ ተጠርጣሪው ለመፈረም ፈቃደኛ ባልሆነ ጊዜ ይህንኑ በመዝገብ ላይ ያሰፍራል፡፡<br>፭. ተጠርጣሪው ቃሉን በማቆያ ቤት የምርመራ ክፍል ወይም ወንጀሉ በተፈጸመበት ቦታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተጠርጣሪው ቃሉን በሚሰጥበት ጊዜ ጠበቃው በምርመራ ክፍሉ ሊገኝ ይችላል፡፡ | እንደሚኖረው አግባብነት ባለው የረቂቅ ሕጉ ክፍል መገለፅ አለበት፡፡ | |
| 18. | <u>አንቀጽ ፻፲፰ ተጠርጣሪን ፍርድ ቤት ማቅረብ</u><br><br>፩. የተያዘ ሰው በፖሊስ ዋስትና ያልተለቀቀ ከሆነ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡ ይህም ጊዜ ተጠርጣሪው ከተያዘበት ቦታ ፍርድ ቤት ለማድረስ አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፡፡<br><br>፪. መርማሪው ፖሊስ በዚህ አንቀጽ መሠረት ፍርድ ቤት የቀረበ ተጠርጣሪ የተያዘው **በበቂ ጥርጣሬ** | የማሻሻያ ምክረ ሃሳቦች፡-<br><br>በ አንቀፅ 118 (2) "በቂ ጥርጣሬ" የሚለው መለኪያ፣ ምክንያታዊ ጥርጣሬ" በሚል ሊተካ ይገባል፡፡<br><br>አንቀፅ 122 (2) በተጠርጣሪው ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት አለመፈፀሙን ለማረጋገጥ በሚያስችልመልኩ ሊስተካከል ይገባል፤<br><br>"፪. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ቃል የሰጠውን ሰው በነፃ ፈቃዱ ቃሉን መስጠቱን መጠየቅ፣ ማረጋገጥና በመዝገብ መመዝገብ እንዲሁም በመያዝ ወይም በምርመራ ሂደት የማሰቃየት፣ የጭካኔ፣ ክብረ-ነክ ወይም አዋራጅ ተግባር ወይም ማንኛውም ሕገ-ወጥ የኃይል | ከላይ በተራ ቁጥር 2 የተገለፀውን ማብራርያ ይመልከቱ<br><br>በማቆያ ቦታ ተጠርጣሪዎች ለከፍተኛ የመብት ጥሰት የተጋለጡና የተለያዩ ጭካኔና ኢሰብዓዊ ድርጊቶች ሲፈጸምባቸው እንደቆየ የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ያሳያል። በተግባር እንደታየው ተጠርጣሪዎች ይህ በደል በሚደርስባቸው ጊዜ የመብት ጥሰቱ እንዲቆም የሚጠይቁበት፣ አጥፊው አካልም ተጠያቂ የሚሆንበት አሰራር አልነበረም። ተጠርጣሪዎችን በመያዝም ሆነ በምርመራ ሂደት የማሰቃየት፣ የጭካኔ፣ ክብረ-ነክ ወይም አዋራጅ ተግባርን ጨምሮ ሕገ-ወጥ የኃይል ድርጊት መፈፀም በሰፊው የተለመደ ተግባር ከመሆኑ አንፃር ፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ቃሉን በነፃ መስጠቱን ከመጠየቅ ባሻገር የተፈፀመበት የጭካኔ፣ ክብረ-ነክ ወይም አዋራጅ ተግባርን ወይም ሌላ ሕገ-ወጥ የኃይል ድርጊት መኖር አለመኖሩን በግልፅ እንዲያረጋግጥ መደረጉ እና እንዲህ አይነት ሕገ-ወጥ ድርጊት ተፈፅሞም እንደሆነ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ትዕዛዝ እንዲያሳልፍ ቢደረግ እጅግ ጠቃሚ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | እንዲሁም መያዙ ለምርመራው አስፈላጊ መሆኑን ለፍርድ ቤቱ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡<br><br>፫. ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በማቆያ ቤት መቆየት ለምርመራው አይረዳም ብሎ ካመነ በዋስትና ይለቀዋል፡፡ ሆኖም የተባለው ድርጊት መፈጸሙ ወይም የተያዘው ሰው ወንጀሉን ስለመፈፀሙ አጠራጣሪ ሲሆን ያለ ዋስትና ሊለቀው ይችላል፡፡<br><u>አንቀጽ ፻፳፪ በፍርድ ቤት የሚሰጥ የተጠርጣሪነት ቃል</u><br><br>፪. ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ቃል የሰጠውን ሰው በነፃ ፈቃዱ ቃሉን መስጠቱን መጠየቅ፣ማረጋገጥና በመዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡ | ድርጊት አለመፈፀሙን ተጠርጣሪውን በመጠየቅ ማረጋገጥና ተጠርጣሪው የሰጠውን ምላሽ በሰነዱ ላይ ማስፈር ይኖርበታል፡፡”<br><br>በተጨማሪም የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ መጨመር አለበት፡<br><br>“፫. ተጠርጣሪው በመያዝ ወይም በምርመራ ሂደት የተፈፀመበት የማሰቃየት፣ የጭካኔ፣ ክብረ-ነክ ወይም አዋራጅ ተግባር ወይም ማንኛውም ሕገ-ወጥ የኃይል ድርጊት መኖሩን ያመለከተ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ስለተፈፀመው ድርጊት ለማረጋገጥና ጥፋተኛውን ተጠያቂ ለማድረግ እንደሁኔታው አስፈላጊውን ትዕዛዝ ይሰጣል ።” | አንቀፅ 122 (2) በተመለከተው አግባብ መሻሻሉ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ (አንቀፅ 5) እና አለም አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች ቃልኪዳን (አንቀፅ 7) እንዲሁም ኢሰብዓዊና አዋራጅ አያያዝና ቅጣት ለማስቀረት በተፈረመው ቃል ኪዳን የተቀመጡ ግዴታዎችን በተጨባጭ ተፈፃሚ ለማድረግ ያግዛል። በተመሳሳይ መልኩ በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 10 የተጠቀሰውን በሕግ ነጻነታቸውን የተገፈፉ ሰዎች ሰብዓዊ በሆነ አያያዝ የመጠበቅ መብት ለማረጋገጥ ይረዳል። ተጠያቂነት እንዲኖር መደረጉም በዚሁ ቃል ኪዳን በአንቀጽ 2(3) (ሀ) የተመለከተውን ሰዎች ለደረሰባቸው በደል ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብትን በማረጋገጥ በተግባር የሚታየውን የመብት ጥሰት በዘላቂነት ለመቅረፍ ያስችላል። |
| 19. | <u>አንቀጽ ፻፲፱ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ</u><br><br>፩. ፍርድ ቤት ምርመራው ያልተጠናቀቀ መሆኑንና ምርመራውን ለማድረግ የተጠርጣሪው በማቆያ ቤት መቆየት አስፈላጊ መሆኑን ሲያምን በአንድ ጊዜ እስከ ፲፬ ቀናት የሚደርስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ሊፈቅድ ይችላል፡፡<br>፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሚፈቀደው ጊዜ የወንጀሉን ክብደት፣ ውስብስብነት፣ የሚፈለገውን ማስረጃ ዓይነትና ብዛት እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ | የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ፡-<br>▪ በ 119 (3) የተቀመጠው አጠቃላይ የምርመራ ጊዜ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ ከ60 (ስልሳ) ቀን ሊበልጥ አይችልም በሚል መስተካከል አለበት፤<br>▪ በ 154 (4) እና በ 204 (1) መሠረት ዐቃቤ ሕግ በምርመራ መዝገቡ ላይ ለመወሰን ከዚያም ክስ ለመመስረት ተከፋፍሎ የተሰጠው ጊዜ ቀርቶ “ዐቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡ ከፖሊስ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ 15 ቀናት ውስጥ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ በመስጠት የሚያስከስስ ከሆነ በዚሁ ግዜ ውስጥ ክስ መመስረት አለበት” በሚል መስተካከል አለበት። | አንቀፅ 119 ከሌሎች ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው የረቂቅ ሕጉ ክፍሎች ጋር ሲነበብ በአጠቃላይ ክስ ለመመስረት የሚወስደው ግዜ **ከ 5 ወራት በላይ** ሊሄድ ይችላል። ማለትም፤<br>-በ አንቀፅ 118(1) መሠረት **በ48 ሰዓታት** ውስጥ ፍርድ ቤት ይቀርባል + በ 119 መሠረት እስከ **4 ወር** የሚደርስ ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ይሰጣል + በ 154(4) መሠረት ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገብ ሲደርሰው በመዝገቡ ላይ ውሳኔ ለመስጠት እንደ ወንጀሉ ክብደት እስከ **10 ቀናት** ሊወስድበት ይችላል + በ 204 (1) መሠረት ዐቃቤ ሕግ ክስ ለመመስረት ከወሰነ ክሱን ለመመስረት እንደ ወንጀሉ ክብደት እስከ **20 ቀናት** ተሰጥቶታል + በ 205 (2) መሠረት ዐቃቤ ሕግ በተሰጠው ጊዜ ክስ ላለመመስረቱ በቂ ምክንያት ካለው ተጨማሪ **10 ቀናት** |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የሚፈቀደው አጠቃላይ የምርመራ ጊዜ በማናቸውም ሁኔታ ከአራት ወር ሊበልጥ አይችልም፡፡<br><br>፬. ምርመራው ተጠናቆ ተጨማሪ ጊዜ የማያስፈልገው እንደሆነ ፍርድ ቤት ተጠርጣሪው በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በዋስትና እንዲወጣ ወይም ዐቃቤ ሕግ በአንቀጽ ፻፶፬ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሠረት ክስ እስከሚመሠርት ድረስ ከሀያ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ በማቆያ ቤት እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡<br>አንቀጽ ፻፵፬ የዐቃቤ ሕግ የመወሰን ሥልጣን<br>፬. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡ በደረሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የተመለከቱትን ውሳኔዎች ለቀላል ወንጀሎች በአምስት የስራ ቀናት፣ ለመካከለኛ ወንጀሎች በሰባት የስራ ቀናት፣ ለከባድ ወንጀሎች በአስር የስራ ቀናት ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡<br>አንቀጽ ፻፶፬ ክስ ስለሚመሠረትበት የጊዜ ገደብ<br>፩. ዐቃቤ ሕግ የምርመራ መዝገቡን ተመልክቶ ክስ ለመመስረት የወሰነ እንደሆነ ክስ ለመመስረት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ እንደወንጀሉ ክብደትና ውስብስብነት በሀያ ቀናት ውስጥ ክስ ይመሠርታል፡፡<br>አንቀጽ ፻፶፭ በጊዜ ገደብ ውስጥ ክስ አለመመሥረት<br>፪. ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ በቀጠሮው ቀን ቀርቦ ክስ ያልመሰረተበትን ምክንያት በቂ ሆነ ካገኘው ክስ ለመመስረት እስከ አስር የስራ ቀናት ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡ | ▪ 205 (2) መሠረት **“አሳማኝ ምክንያት”** ሲኖር ሊሰጥ የሚችለው ተጨማሪ ጊዜ በ 5 ቀናት ብቻ መወሰን አለበት። | ሊሰጠው ይችላል። (**48 ሰዓት** + **4 ወር** + **10 ቀናት** + **20 ቀናት** + **10 ቀናት በአጠቃላይ ከ 5 ወራት በላይ ይሆናል**)፡፡<br>ይህ ሁኔታ የተጠርጣሪውን የተፋጠነ ፍትህ የማግኘት መብትን በእጅጉ ይጎዳል፡፡ በመሆኑም፤<br><br>በረቂቅ ሕጉ በአጠቃላይ ክስ ለመመስረት የሚወስደው ግዜ ከ 5 ወራት በላይ ሊሄድ የሚችል መሆኑ በተለይ ተጠርጣሪው ተይዞ የአካል ነፃነቱ እና የመንቀሳቀስ መብቱን ባጣበት ሁኔታ ክስ ሳይመሰረትበት ለረጅም ግዜ እንዲቆይ መደረጉ በኢፌዲሪ ሕገ መንግስትና በአለም አቀፍ ስምምነቶች መሠረት የተረጋገጡትን የተፋጠነ ፍትሕ የማግኘት መብትን ጨምሮ የተያዙ ሰዎችን መብቶች የሚፃረር ነው።<br><br>በመሆኑም በ 119 መሠረት የሚሰጠው ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ በድምሩ 4 ወር ሳይሆን ከ 60 ካላንደር ቀኖች እንዳይበልጥ መገደቡ ተገቢ ነው።<br><br>የምርመራ መዝገቡን ተመልክቶ ለመወሰን እና ክስ ለመመስረት ለዐቃቤ ሕግ የሚሰጠውን ጊዜ በተመለከተ አሁን ስራ ላይ ባለው የስነ ስርአት ሕግ በአንቀጽ 109(1) መሰረት ዐቃቤ ህግ የምርመራ መዝገቡ ከፖሊስ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ 15 ቀናት ውስጥ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ በመስጠት የሚያስከስስ ከሆነ በዚሁ ግዜ ውስጥ ክስ መመስረት እንዳለበት ተደንግጎ ይገኛል። ረቂቅ ሕጉ የተሻለ አሠራር መደንገግ ሲገባው በሥራ ላይ ካለው ሕግ ይበልጥ የተራዘመና የተያዙ ሰዎችን መብቶች የሚጎዳ አሰራር ማስቀመጡ ተገቢ አይደለም።፡ የተፋጠነ ፍትሕን ለማረጋገጥና የተያዙ ሰዎችን መብት ለማስከበር ሊስተካከል ይገባል። በተመሳሳይ ምክንያት ዐቃቤ ሕግ በተሰጠው ጊዜ ክስ ላለመመሥረቱ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር ሊሰጥ የሚችለው ተጨማሪ ጊዜ በ 5 ቀናት ብቻ መወሰን ተገቢ ነው።<br>በረቂቅ ሕጉ የተቀመጡትን ቀናት ማሳጠር የሚያስፈልግበት ዋነኛው ምክንያት ተጠርጣሪው ተይዞ የአካል ነፃነቱን እና የመንቀሳቀስ መብቱን ያጣ በመሆኑ ነው። ፖሊስ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ምርመራውን አለማጠናቀቁ ወይም ዐቃቤ ሕግ ክስ አለመመስረቱ ውጤቱ በዚህ ምክንያት የወንጀል ምርመራው ወይም |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | ክሱ ቀሪ ሆኖ ተጠርጣሪው በነፃ ይሰናበታል ማለት ሳይሆን ተጠርጣሪው በዋስትና ወይም ያለዋስትና ተለቆ ምርመራውም ሆነ ክሱም መቀጠል የሚችል እንደመሆኑ፤ ተጠርጣሪ ተይዞ ለሚደረግ ምርመራ እና ክስ የተገደበ ጊዜ መስጠቱ ተገቢ ነው። ገና ጥፋተኝነቱ ያልተረጋገጠ ተጠርጣሪ ክስ ሳይመሰረትበት ለረጅም ጊዜ ተይዞ እንዲቆይ መደረጉ የተፋጠነ ፍትሕን ከማጓደሉም በላይ የቅጣት አይነት ባህርይ ስላለው የተጠርጣሪውን ከፍርድ በፊት ንፁህ ሆኖ የመቆጠር መብት የሚቃረን ነው። |
| 20. | <u>ምዕራፍ ሦስት የንብረት እግድና አስተዳደር</u><br><br>አንቀጽ <u>፻፳፫</u>-<u>፻፳፰</u> | የንብረት እግድ የሚመራበት ሥርዓት በግልፅ መቀመጥ ይኖርበታል። | ስለ ንብረት እግድ በረቂቅ ሕጉ የቀረበው ንብረትን አላግባብ/በዘፈቀደ ሊያሳጣ የሚችል ነው። ሕጉ የእግድ ውሳኔ ከመደረጉ በፊት የተከሳሹን የመሰማት መብት ለማረጋገጥ የሚያስችል አግባብነት ያለው አሰራር ሊያስቀምጥ ያስፈልጋል። እግዱ በጊዜ የተገደበ ሊሆን ይገባል፤ የእግድ ውሳኔውም እግዱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ማሳወቅ አለበት። እግዱን አስፈላጊ ያደረገው ምክንያት ሲቀር እግዱም አብሮ ማብቃት አለበት። |
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 21. | <u>አንቀጽ ፻፵፪ ዋስትናን መፍቀድ</u><br><br>፩. ፍርድ ቤት በዋስትና ግዴታ የመለቀቅ ጥያቄውን የተቀበለው እንደሆነ ተጠርጣሪው ወይም ተከሳሹ የሚለቀቅበትን የዋስትና ግዴታ ዐይነትና መጠን መወሰን ይኖርበታል፡፡<br>፪. ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ልጅ ያላቸው ባልና ሚስት በተመሳሳይ ወይም አንድ ላይ የተያዙ እንደሆነ ለልጆቹ አስተዳደግ የበለጠ ይጠቅማል ለተባለው የዋስትና መብት መፈቀድ ይኖርበታል፡፡<br>፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ፍርድ ቤቱ የሚወስነው የዋስትና ግዴታ የራስ ዋስትና፣ የገንዘብ፣ የሰው ወይም የንብረት ዋስትና ግዴታ ሊሆን ይችላል፡፡ | ከንዑስ አንቀፅ ፪ ተከትሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ ፫ ሊጨመርና፣ ንዑስ አንቀፅ ፫ የነበረው ንዑስ አንቀፅ ፬ ሆኖ ሊስተካከል ይገባል፤<br>፫. ነፍሰ ጡር ለሆነች ሴት ወይም ከዘጠኝ አመት በታች የሆነ ሕፃን ወይም የምትንከባከበው የአካል ጉዳተኛ ልጅ ላላት እናት በልጅዋ ወይም ልጆችዋ ላይ ጉዳት እንደማታደርስ ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ከሌለ በቀር ዋስትና ወዲያውኑ መፈቀድ አለበት። | ኮሚሽኑ በተለያዩ ጊዜያት በማረሚያ ቤቶች ተዘዋውሮ ባደረገው ክትትል ሴቶች ከሕፃናት ልጆቻቸው ጋር በእስር የሚቆዩበት ሁኔታ መኖሩን ለመረዳት የቻለ ሲሆን ከችግሩ አሳሳቢነት አንፃር ሕፃናትን የማሳደግ ኃላፊነት ያለባቸው ወይም ለአካል ጉዳተኛ ልጃቸው እንክብካቤ የሚያደርጉ ሴቶች ወዲያውኑ ዋስትና የሚያገኙበት አሠራር ሊኖር ይገባል። ምንም እንኳን 18 አመት ያልሞላቸው ልጆች በኢትዮጵያ ሕግ ለአካለ መጠን ያልደረሱ እና የወላጆቻቸው እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው ቢሆንም ከዚያ ይልቅ ልጆች በወንጀል ሕግ የወንጀል ኃላፊነት መውሰድ የሚጀምሩበትን (ወጣት ጥፋተኝነት) እድሜ መሠረት በማድረግ ቢያንስ ዘጠኝ አመት ያልሞላው ህፃን የሚያሳድጉ እናቶች ወዲያው የዋስትና ተጠቃሚ ቢሆኑ ምክንያታዊ ይሆናል። ይህም ሕፃናት ከእናቶቻቸው ጋር የሚታሰሩበትን አሳሳቢ ሁኔታ በማስቀረት የልጆችን ሰብአዊ መብቶችን ጭምር ለማስከበር ያስችላል። በተጨማሪም ይህንኑ የዋስትና መብት የምትንከባከበው የአካል ጉዳተኛ ልጅ ላላት እናት ማረጋገጥ በአካል ጉዳት ምክንያት ልዩ እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ልጆች መብቶች የሚያስከብር ጠቃሚ እርምጃ ነው። ምክረ ሃሳቡ ከሰብዓዊ መብቶች የሕግ ማዐቀፍ አንጻር ሲታይ ህጻናትን ከተጠርጣሪ እናት ጋር በማቆያ ቦታ ወይም በእስር ቤት ማቆየት በተ.መ.ድ. የህጻናት መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 37 (ለ) የተመለከተውን የህጻናትን በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት አለአግባብ የሚጥስ በመሆኑ የተጠቀሰው ድንጋጌ በረቂቅ ሕጉ ሊካተት ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ በአፍሪካ የህጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 30 (ሀ) እንደተመለከተው የወንጀል ሃላፊነት ያለባቸው እናቶች በተቻለ አቅም ከእስር ውጭ ባሉ አማራጭ ቅጣቶች ሊቀጡ እንደሚገባ የሚደነግግ ሲሆን፣ ይህም በዋስትና አስጣጥ ሥርዓት ላይ ተፈጻሚነት ያለው በመሆኑ ምክረ ሃሳቡ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 22. | <u>የጥፋተኝነት ድርድር</u><br><br>አንቀጽ <u>የ፷፱</u> - <u>የ፸፱</u> | በረቂቅ ሕጉ የተቀመጠው የጥፋተኝነት ድርድር ሥርዓት በሰፊው የተቀረፀ (ያልተገደበ) እንደመሆኑ የሚከተሉት ማስተካከያዎች ሊደረጉበት ይገባል፤<br>-የጥፋተኝነት ድርድር በሁሉም ወንጀሎች ላይ ተፈፃሚ የሚሆን አይደለም፡፡ ስለሆነም ተፋፃሚ የማይሆንባቸው ወንጀሎች (ለምሳሌ፡ በዘር ማጥፋት የመሰሉ ከባድ ወንጀሎች) ተለይቶ ሊገለጽ ይገባል፡፡<br>-የፍሬ ነገር እና የክስ አይነት (ብዛት) ድርድርን ባይጨምር (በቅጣት መጠን ድርድር ላይ ቢወሰን)<br>-የሚቀነሰው የቅጣት መጠን ቢወሰን<br>-ፍርድ ቤት በአጠቃላይ የድርድር ሂደቱንም ሆነ ይዘቱን በጥልቀት የመገምገም ሚና እንዲኖረው ቢደረግ | በሰፊው የተቀረፀ (ያልተገደበ) የድርድር ሥርዓት ላልተገባ አሰራር እና ለመብት ጥሰት የተጋለጠ ነው። ይህ አሰራር እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ያልዳበረ የፍትሕ ሥርዓት ያላቸው ሃገሮች ቀርቶ ጠንካራ የፍትሕ ሥርዓት ባላቸው አገሮች ጭምር ሙስናን ጨምሮ ለብልሹ አሰራሮች እና አላግባብ የሆነ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና ሌሎች የተከሳሽ መብቶች ጥሰቶች ስለማስከተሉ ጥናቶች ያሳያሉ። የተወሰኑ ከባድ ወንጀሎችን በተመለከተ ከተቀላጠፈ አሰራር ይልቅ እውነትን ማወቅና ማረጋገጥ ስለሚያይል ከጥፋተኝነት ድርድር ወጭ መደረጋቸው ተገቢ ነው። የፍሬ ነገር እና የክስ አይነት (ብዛት) ድርድር ለብልሹ አሰራሮች መንገድ ስለሚከፍት ቢቀር ይመረጣል። የቅጣት መጠን ድርድርም ቢሆን በሕግ በተቀመጡ ገደቦች ቢወሰን ጠቃሚ ነው። ተከሳሹ በአንዳንድ ሁኔታዎች በቅጡ ሳያስብበት በተለይም የተራዘመ የቅድመ-ክስ/ቅድመ-ፍርድ እስር ለማስቀረትና በቶሎ ለመለቀቅ በሚል ጥፋተኝነቱን ተቀብሎ ወደ ድርድር ሊገባ ይችላል፤ በዚህም አላግባብ ፍትሃዊ ዳኝነት የማግኘት መብቱ ሊጣስ ይችላል። በተላይ የተራዘመ የቅድመ-ክስ/ቅድመ-ፍርድ እስር በተለመደበት ሃገር ፖሊስ/አቃቤ ሕግ እስርን ለድርድር የሚጠቀሙበትን ሁኔታን በመፍጠር የመብት ጥሰቶችን ሊያስከትል ይችላል። በአጠቃላይ ፍርድቢቤት የድርድር ሂደቱንም ሆነ ይዘቱን በጥልቀት የመገምገም ሚና እንዲኖረው መደረጉ የመብት ጥሰቶችንም ሆነ ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ተገቢ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 23. | <u>ባህላዊ ሥርዓቶች</u><br><br>አንቀጽ <u>፻፹</u>- <u>፻፹፯</u> | አግባብነት ባላቸው የረቂቅ ሕጉ ክፍሎች የሚከተሉት ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል፤<br><br>-የትኞቹ የወንጀል ዓይነቶች በባህላዊ ሥርዓት ሊዳኙ እንደሚችሉ በተሻለ ሁኔታ ግልፅ ማድረግ<br>-ባህላዊ ሥርዓትን በማስጀመርም ሆነ ሂደቱን በመቃወም ረገድ የተከሳሾች እና ተበዳዮች ሚና እና ያላቸው መብቶች በግልፅ ማስቀመጥ<br>-በባህላዊ ሥርዓት የሚወሰኑ ውሳኔዎችን በተመለከተ የፍርድ ቤቶችን ሚና ማሳደግ። በአንቀፅ 187 ፍርድ ቤት በባህላዊ ሥርዓት የተወሰነውን ወሳኔ “እንዲመዘገብ ያደርጋል፣ መዝገቡንም ይዘጋል” የሚለው ማሻሻያ ማድረግ፡ ያስፈልጋል፡ | የባህላዊ ሥርዓቶች ቦታ መሰጠቱ መልካም ሆኖ እነዚህ ሥርዓቶች በተጠርጣሪዎችና ተበዳዮች መብቶች ላይ ሊያሳድሩ ከሚችሉት አሉታዊ ተፅዕኖዎች አንፃር ማሻሻያዎቹ ቢደረጉ ጠቃሚ ነው። በአንቀፅ 181(2) “ሰብዓዊ መብትን የሚጥስ፣ በሠው ልጅ ክብር እና በሀገር ደህንነት ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች የተጠረጠሩ ወይም የተከሰሱ” ሰዎችን በተመለከተ ባህላዊ ሥርዓቶች ተፈፃሚነት እንደማይኖራቸው ቢገለፅም ይህ ሃረግ በራሱ ግልፅ ያልሆነና ለትርጉም የተጋለጠ ነው። ባህላዊ ሥርዓትን በማስጀመርም ሆነ ሂደቱን በመቃወም ረገድ የተከሳሾች እና ተበዳዮች ሚና እና ያላቸው መብቶች በግልፅ መቀመጡ ፍትሕን ከማረጋገጥና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ከመከላከል አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል። ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ የተቋቋሙ ዋነኛዎቹ የፍትሕ አስከባሪ ተቋማት እንደመሆናቸው በባህላዊ ሥርዓት የተወሰኑ ወሳኔዎችን መዝግቦ መዝገብ ከመዝጋት ያለፈ ሚና ሊኖራቸው ያስፈልጋል። ፍትሕን ለማረጋገጥና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ሲኖሩ ማስተካከያዎችን ለማድረግ እንዲቻል ፍርድ ቤቶች አቤቱታ መቀበልን ጨምሮ የተሻለ ሚና ሊኖራቸው ይገባል። |
| 24. | <u>አንቀጽ ፪፻፹፫ በቅድመ ክስ መስማት የሚከናወኑ ተግባራት</u><br>(ረ) የተከላካይ ጠበቃ፣ አስተርጓሚ፣ ለፍትሕ አሰጣጥ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ባለሙያዎችን አስቀድሞ እንዲሟሉና እንዲታወቁ የማድረግ፣ | መስማት የተሳናቸውን ፍትሕ የማግኘት መብት ለማስከበር ይቻል ዘንድ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ የሚል ሊጨመርበት ይገባል፡፡ | ኮሚሽኑ በነሐሴ 2012 ከአካል ጉዳተኞች ማህበር ጋር ባደረገው ፈጣን ዳሰሳ የፍትሕ አካላት ፍርድ ቤትን ጨምሮ ፍትሕን መስማት ለተሳናቸውና የአዕምሮ ጉዳተኞች ተደራሽ ለማድረግ የምልክት ቋንቋና ሌሎች ባለሙያዎች እንደማይጠቀም አሳይቷል።<br>አባሎቻቸውን ለመደገፍ የአካል ጉዳተኞች ማህበር አቅም በፈቀደ መልኩ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ የሚመድብ ቢሆንም ይህ የአካል ጉዳተኞችን የፍትሕ አገልግሎት መብት የሚነፍግ በመሆኑ የፍርድ ቤቱ ኃላፊነት ሆኖ መቀመጡ ተገቢ ነው፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 25. | አንቀጽ ፪፻፴፱ ችሎቱ ክሱን በንባብ ከማሰማቱ በፊት፡-<br>(ለ) የቅድመ ክስ መስማት ተግባራት ከንውን መሠረት አድርጎ በተለይም የአስተርጓሚ እና የጠበቃ ጉዳይ እንደአስፈላጊነቱ መሟላቱን ያረጋግጣል፡፡ | ከላይ በተጠቀሰው መልኩ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ እንደአስፈላጊነቱ መሟላቱን ያረጋግጣል በሚል መካተት አለበት፡፡ | ከላይ ከተሰጠው ሃተታ ዘምክንያት ወይም ማብራሪያ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 26. | <u>አንቀጽ ፻፶፯ ቅጣት እንዲፈፀም የሚሰጥ ትእዛዝ</u> | የቅጣት አፈፃፀምን በተመለከተ ከተቀመጡት ንዑስ አንቀፆች በመከተል (ወይም ሌላ አግባብነት ባለው ቦታ) የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ ፫ መጨመር አለበት፡፡<br>፫. ፍርደኛው ከፍርድ ወይም ከቅጣት ውሳኔ በፊት በማቆያ ወይም ማረፍያ ቤት በእስር ያሳለፈው ጊዜ ከተወሰነበት ቅጣት የሚቀነስበት አሠራር በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡ | ይህ ማሻሻያ መደረጉ በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 23 እንዲሁም በረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 6 በአንድ ወንጀል ድጋሚ **ቅጣት ከመከልከሉ** (prohibition of double jeopardy) ጋር የሚያያዝ እንዲሁም የተ.መ.ድ. ሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ የተያዙ ሰዎችን መብት በተመለከተ ባወጣው አጠቃላይ አስተያየት General Comment 35 ከፍርድ በፊት ቅጣታቸውን የፈፀሙ ሰዎችን በተመለከት የሰጠውን ምክረ ሃሳብ ለማስፈፀም የሚያስችል ነው። |
| 27 | <u>አንቀጽ ፻፶፰ የእስራት ቅጣት ማስተላለፍ</u><br><br>፩. የእስራት ቅጣት አፈፃፀም ጊዜ፣<br><br>(ለ) አስራ ስምንት ወር ያልሞላው ሕጻን ያላት እናት ስትሆን ሕጻኑ ሠላሳ ወር ወር እስኪሞላው ድረስ፣<br><br>(ሐ) ነፍሰ ጡር እንደሆነች የእርግዝና ጊዜው እስከሚያበቃና ከወለደች በኋላ ሠላሳ ወር እስኪሆነው፣ | የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ሊሰረዙ እና በዚህ ሰንጠረዥ በቁጥር 21 እና 28 ስር በተመለከተው መሰረት ሊስተካከል ይገባል። | በቁጥር 21 ላይ ህጻናት ከእናታቸው ጋር ሊታሠሩ አይገባም በሚል የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ።<br><br>ምክረ ሃሳቡ በተለይም የአፍሪካ ህጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር በአንቀጽ 30 (ሀ) ላይ እንደተመለከተው ፍርደኛ እናቶች ከእስር ውጭ ባሉ አማራጭ ቅጣቶች ሊቀጡ ይገባል በሚል ያስቀመጠውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ነው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 28 | <u>አማራጭ ቅጣት</u><br><br><u>አንቀጽ ፻፫ መርህ</u><br><br>፩. ፍርድ ቤት በራሱ አስተያየት ወይም በፍርደኛው ጥያቄ በዚህ ሕግ በተደነገገው መሠረት በዋና ቅጣት ምትክ አማራጭ ቅጣትን መወሰን ይችላል፡፡ በሕግ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የሚወሰነው አማራጭ ቅጣት በስራ ወይም በግዴታ ሥራ የሚፈጸም ይሆናል፡፡<br><br>፪. ፍርድ ቤት አማራጭ ቅጣት የሚወስነው የቅጣት ዓላማን ይበልጥ ያሳካል ብሎ ሲያምን እና ፍርደኛው፡-<br><br>(ሀ) ጥፋተኛ የተባለበት ወንጀል ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም በገንዘብ ብቻ የሚያስቀጣ ወይም ከሦስት ዓመት በማይበልጥ በቀላል እስራትና በገንዘብ የሚያስቀጣ ወንጀል ከሆነ፣<br><br>(ለ) ጤንነቱ ተመርምሮ የጉልበት ሥራ መሥራት መቻሉ ሲረጋገጥ፣ እና<br><br>(ሐ) ከእስራት ይልቅ በጉልበት ሥራ ቢቀጣ ለሕብረተሰቡ አደገኛ አለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡<br><br>፫.አማራጭ ቅጣት ተፈጻሚ የሚሆነው በተፈጥሮ ሰው ላይ ብቻ ይሆናል፡፡ | ከታች የተመለከተው ተጨማሪ ድንጋጌ ሊካተት ይገባል፤<br><br>“ፍርደኛዋ የህጻን ልጅ እናት ከሆነችና ወንጀሉ በእስራት የሚስያቀጣ ከሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከእስር ውጭ ያለ አማራጭ ቅጣት እንዲፈጸም ሊያዝ ይችላል።” | ከላይ በተራ ቁጥር 21 እና 27 የመለከተውን ማብራሪያ በተለይም የአፍሪካ ህጻናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር አንቀጽ 30(ሀ)ን ይመልከቱ። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29 | አንቀጽ ፫፻፴፱ ይግባኝ የሚባልባቸው ጉዳዮች<br>፩. በዚህ ሕግ ሌሎች ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን፡-<br>**(ለ)** የተከሳሽ የዋስትና መብትን በመፍቀድ ወይም በመከልከል በሚሰጥ ውሳኔ፣ | በአንቀጽ ፫፻፴፱ (1) (ለ) የተመለከተው የተከሳሽ የዋስትና መብትን በመፍቀድ የተሰጠ ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የማቅረብ መብት ቀሪ ሊደረግ ይገባል። | በመሰረቱ በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 19 (6) ላይ እንደተመለከተው ምንም እንኳ ፍጹም ባይሆንም የተያዙ ሰዎች በዋስትና የመለቀቅ ሕገ መንግስታዊ መብት አላቸው። በዋሰትና የመለቀቅ መብት መርህ ሲሆን አለመለቀቅ ደግሞ በተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ ተፈጻሚነት ያለው ነው። ስለሆነም በዋስትና መለቅቅ ጉዳይ ላይ አቃቤ ሕግ የተሰጠው ይግባኝ የማለት መብት ይህን በሕገ መንግስት ልዩ ጥበቃ የተደረገለትን መብት ተግባራዊ አፈጻጸም በእጅጉ ሊያጣብብ የሚችል በመሆኑ በምክረ ሃሳቡ መሰረት ድንጋጌው ሊስተካካል ይገባል። ከዚህም በተጨማሪ ድንጋጌው በዚህ መልኩ ቢስተካካል በረቂቅ ሕጉ የተመለከተው ከጥፋተኝነት ፍርድ በፊት የሚደረግ መያዝና እሰርን የማስቀረት መርሆን የሚያበረታታ ይሆናል። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 30 | <u>አንቀጽ ፩፻፵ ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮች</u><br><br>(መ) ተከሳሹ ጥፋቱን ያመነ እንደሆነ በእምነት ቃሉ መሠረት የተሰጠ የጥፋተኝነት ውሳኔ፣<br><br>(ሠ) ተከሳሽ በሌለበት በተወሰነ ጉዳይ ወደ ክርክር እንዲገባ በቀረበ ጥያቄ በሚሰጥ ትእዛዝ፤ | በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ የተጣለው ይግባኝ የማቅረብ ክልከላ ሙሉ በሙሉ ሊነሳ ይገባል፡፡ | በረቂቅ ህጉ በአንቀጽ ፩፻፴፮ የይግባኝ ዓላማዎች ውስጥ "በሥር ፍርድ ቤት የተፈጸመ የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ስሕተትን ለማረም"፤ እና ወጥ ወይም ተቀራራቢ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ለማድረግ" የሚሉት ይገኙባቸዋል።<br>በመሆኑም የፍርድ ሂደትን ይግባኝ የማለት ሂደት የሰዎችን የወንጀል ሃላፊነት ከመወሰን ባለፈ የጠቅላላ የወንጀል ስርዓቱን ፍትሃዊነት፣ ጥራትና ወጥነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥቅም ያለው በመሆኑ በተለይ ከተከሳሹ መብት አንጻር ይግባኝ የሚባልባቸው ጉዳዮች በጠበቡ ቁጥር ይህን አገራዊ ፖሊሲ ለማሳካት ያለውን እድል ያጠባል።<br>በሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 14 (3) (ሰ) እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ እንዲመሰክር ወይም ጥፋተኛነቱን እንዲያምን ያለመገደድ መብት እንዳለው ይደነገጋል።<br>በኢትዮጵያ ካለው እጅግ አነስተኛ የህግ ግንዛቤ አንፃር በተለይም የህግ አማካሪ መቅጠር የማይችሉ ወይም በመንግስት ወጪ ተከላካይ ጠበቃ ያልተመደበላቸው ተከሳሾች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር በመሆኑ የወንጀል ስርዓቱ ኢፍትሃዊ እንዲሆን ያደርገዋል። በተጨማሪም በተከሳሽ የእምነት ቃል የተሰጠን ፍርድ ይግባኝ የማይባልበት ጉዳይ እንደሆነ ክልከላ መጣል ለረጅም አመታት የፍትህ ስርዓቱ ሲወቀስበት የነበረውን ተጠርጣሪዎችን በድብደባ፣ በማስፈራራት ወይም በማታለል የእምነት ቃል እንዲሰጡ የማደረግ ህገ ወጥና ኢሰብዓዊ አሰራር ከማስወገድ ይልቅ የበለጠ የሚያበረታታ ሊሆን ይችላል።<br>በሌላ በኩል ተከሳሽ በሌለበት በተወሰነ ጉዳይ ወደ ክርክር እንዲገባ በቀረበ ጥያቄ በሚሰጥ ትእዛዝ ላይ የይግባኝ መብት መከልከሉ ተከሳሹ/ፍርደኛው የመሰማት እና በተገኘበት የመዳኘት መብቱን ባልተጠቀመበት ሁኔታ የተሰጠን ፍርድ የሚያፀና እንደመሆኑ ክልከላው ኢፍትሃዊ ይሆናል።<br>በአጠቃላይ በይግባኝ መብት ላይ የሚጣሉ አግባብነት የሌላቸው ክልከላዎች የተከሳሹን በኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 37 የተረጋገጠውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጥሱ ናቸው። |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 31 | አንቀጽ ፩የ፲ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለን ሰው በጊዜያዊነት የማስተላለፍ ትብብር | በዚህ ድንጋጌ ወይም በተከታዮቹ ድንጋጌዎች ማንኛውም ሰው ከፍ ያለ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሊደርስበት ይችላል ተብሎ ወደሚገመት ሃገር ያለመተላለፍ ጥበቃ እንደሚደረግለት ሊገለጽ ይገባል፡፡ | የተ.መ.ድ. የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ የአለም አቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች ቃልኪዳን አባል ሃገራት በስምምነቱ አንቀፅ ሁለት መሠረት ያላቸው በግዛታቸው እና በቁጥጥራቸው የሚገኙ ሰዎችን ሰብአዊ መብቶች የማክበር እና የማስጠበቅ ግዴታቸው በሰዎች ላይ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች በተለይም በህይወት የመኖር መብታቸው ወይም ከማሰቃየት ወይም ኢሰብአዊ አያያዝ የመጠበቅ መብታቸው አደጋ ላይ ወደሚወድቅባቸው ሃገራት ያለማስተላለፍ ኃላፊነት እንደሚጥልባቸው በሰጠው አጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 31 ላይ ይገልፃል። |